# የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን 125ኛ ዓመት መታሰቢያ መጽሔት

## ወርቃማ ዕፁብ ድንቅ ንግግር

-በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ።
እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የእነዚያን ሁሉ ክርስቲያን ደም በከንቱ መፍሰሱን እያየው ድል አደረጉኋቸው ብዬ ደስ አይለኝም። አጤ ምኒልክ ጣሊያንን ድል ባደረጉ በወሩ ለአውሮፓዊው ዲፕሎማት ለሙሴ ሽፍኔ ከጻፉለት÷÷÷÷

ሙሉ ታሪኩን ዝክረ ምኒልክ ወጣይቱ ላይ ያንብቡ።

www.ethiopianorthodox.org

# ዝክረ ምኒልክ ወጣይቱ



*አፄ ምኒልክና ብልህዋ እቴጌ ጣይቱ*

ንጉሠ ነግሥት አፄ ምኒልክ ይላል ኢንሳክሎፒዲያ ብሪታኒካ *«ዘመናዊቷንና ታላቋን በጠላት የማትደፈር ሉዓላዊት ኢትዮጵያን የፈጠሩ ሰው ናቸው»* ስለ እምዬ ምኒልክ የአስተዳደር ብልሃት፣ ጀግንነት፣ ሥራ ወዳድነት፣ የአገር ፍቅርና እንዲሁም ለስልጣኔና ለእድገት ስላላቸው ጉጉትና ቁርጠኛነት ብዙዎች የሀገር ውስጥና የውጭ ጸሐፍት በየማስታወሻዎቻቸው ዘግበውልን አልፈዋል፣ እነዚህ ጸሐፍት ጽፈው ካቆዩልን ጥቂቱን፦ እ ኝህን ሀገር ወዳድና ጀግና ንጉሥ ከብልኋ ባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በዚህ መጽሔት ልንዘክራቸው ወደድን፤

## *ምኒልክና የክፉው ቀን ረሃብ*

ምኒልክ ባላንጣዎቻቸውን ለማረጋጋትና አገሪቱን ለማደላደል በሚራወጡበትና በሚደክሙበት ጊዜ በኢትዮጵያ ከባድ ረሃብ ደረሰ። ይህ የረሃብ ዘመን ከ1880 ዓ.ም እስከ 1884 ዓ.ም ድረስ ለአምስት ዓመታት ያህል ቆየ። በነዚህ ዘመናት ይህ ረሃብ ሊደርስ የቻለው የከብት በሽታ ገብቶ ከብቱን ስለጨ ረሰው ነበር። በደረሰው የከብት ማለቅ ምክንያት ከዳር እስከዳር ያለው የእርሻ ተግባር ቆመ፣ በገበያም ላይ የእህል ዘር አልታይ አ ለ። ከረሃቡ በፊት በአንድ ማርትሬዛ ብር 20 ቁና ስንዴ ይገዛ የነበረው በ ረሃቡ ወቅት ሊያውም በድብቅ በአንድ ማርትሬዛ ብር አንድ ቁና ስንዴ ይሸመት ጀመር። ረሃቡ ስለጠናም ሕዝቡ በብዛት ያልቅ ጀመር። ረሃቡ በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆነ የሕዝቡ እልቂትም በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር።

ሕዝቡም፦ *እህል
ታሟል አሉ ሄደን እንየው፣
የማይተርፍ እንደሆነ እኛ
እንቅደመው
እህል ካበለለ ሄደ በንፋስ፣
ተከተለው በሬ እንዳይመለስ።*
እያለ ያለቅስ ጀመር።

በአፄ ምኒልክ ዘመን ስለደ ረሰው ረሃብ ብዙ የሀገር ውስጥና የውጭ አገር ጸሐፍት ስለ ረሃቡ አስከፊነት ያዩትንና



www.ethiopianorthodox.org

የታዘቡትን እንዲህ ገልፀውታል።

በዘመኑ የውጭ ሃገር ሚስዮናዊ የነበሩት አባ ሚካኤል አረጋዊ በፃፉት ደብዳቤ:- በትግሬ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች አልቀዋል፣ የገባው ረሃብ ከባድ በመሆኑ ድሆችም ሀብታሞችም በመሞት ላይ ናቸው....ልጆቼ /ተማሪዎቼ/ ከዱር ውስጥ ያገኙትን ፍሬ ሲለቅሙ ይውሉና ያገኙትን ቀቅለው ያቼን እንቀምሳለን። የሞተ አውሬ ሲገኝ አንዳንድ ሰዎች ያን ሥጋ ይበሉና ይሞታሉ። ይህ ረሃብ ያደረሰውን ነገር በሙሉ ልፅፍልህ አልችልም....» ብለዋል።

ፈረንሣዊው ሐኪም ውርዝ በበኩሉ በግል ማስታወሻው ላይ ረሃቡን እንደሚከተለው ገልጾታል«... በአገሪቱ ላይ ያሉ ከብቶች በሙሉ አልቀዋል፣ ለምሣሌ በቡልጋ ያሉ ከብቶች ያለቁት በ8 ቀን ውስጥ ነው። በዚያም ምኒልክ የነበሯዋቸው ከብቶች አንድም ሣይተርፉ ሁሉም ሞቱ። እንደሚነገረው ያለቁት የምኒልክ ከብቶች 250,000 ያህል ናቸው ይባላል።»

ኢትዮጵያዊው ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ በመጽሐፋቸው «....ሰው የጅብ ሥጋ መብላቱንና በአንዳንድ ጠቅላይ ግዛቶችም ሰው የሰው ሥጋ መብላቱን ጽፈዋል።» የምኒልክ ፀሐፊ ትዕዛዝ የነበሩት አለቃ ገ/ሥላሴም:-«....ጉኑ ረሃብ ሆነ፣ የፈረሥ ሥጋ፣ የአህያ ሥጋ ተበላ። ሰው ሰውን በላው፣ በወሎም አንዲት ሴት ልጆዋን በላች፣ እንሳሮ በሚባል አገርም አንዲት ሴት ሰባት ሕፃናት በላች.....»በማለት ጽፈዋል። ይህ ረሃብ እንደደረሰ አፄ ምኒልክ ማንም ሰው የላም ሥጋ እንዳይበላ ወይም እንዳያርድ በአዋጅ አስከለከሉ። በቤተ መንግሥቱም ቢሆን አንድም የቀንድ ከብት እንዳይታረድ ተከለከለ። አብዛኛው የቤተ መንግሥት ግብርም በንፍሮ በእንጀራና በእህል ወጥ ብቻ ሆነ። ከቤተ መንግሥቱ ለሚጠጋው ረሃብተኛም ንፍሮ በብዙ ጋኖች ተቀቅሎ እያደረ በነጋታው ምኒልክ ራሳቸው ለሕዝብ በማደሉ ተግባር ይካፈሉ ጀመር።

ከረሃቡ መፅናት የተነሣ በእንሳሮ አንዲት ሴት ሰባት ሕፃናትን በላች የሚለው ወሬ ከምኒልክ ጆሮ ደረሠ። በአስቸኳይም ተይዛ እንድትመጣ አዘው፣ መጥታ ከፊታቸው ስትቀርብ «እውነት የሰው ሥጋ በላሽን» ብለው ጠይቋት እሷም:-«አዎን! ጃንሆይ ቢርበኝ ሰባት ልጆችን ይዤ በላሁ» አለቻቸው። እሳቸውም:-«ከወዴት እየያዝሽ፣ እንዴትስ እያደረግሽ ገደልሽና በላሻቸው» ብለው ቢጠይቋት «ከሚጫወቱበት ቦታ እያነቅሁ እየያዝሁ ነው» በማለት መለሰችላቸው። በዚህ መልሷ ምኒልክ:- «እንዴት አገሬ ጠፋ፣ ድሃዬ አለቀ ብለው ማልቀሳቸውን» ፕሮፌሰር አፈወርቅ ጽፈዋል።

ከብት አልቆ የሚታረስበት መጥፋቱን ያዩት አፄ ምኒልክ የከብት ነገር ተፈፅሞ አልቋልና እግዜር ፊቱን እስኪመልስልን ድረሥ እኔም አብነት ለመሆን ብዬ በእጄ የምቆፍርበትን ዶማ፣ የምቆርጥበት መጥረቢያ አዘጋጅቻለሁና እናንተም እንደእኔ ሁኑ እያሉ ለየመኳንንቱ ደብዳቤ ፅፈው፣ ለእያንዳንዱም አንዳንድ ትናንሽ ዶማና መጥረቢያ ላኩላቸው፣ መጀመሪያ የተላከላቸው የጐጃም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት፣ የወሎው ራስ ሚካኤልና የጐንደሩ የራስ ወሌ ነበሩ።

ምኒልክ ለአብነት እሆናለሁ ባሉት ቃል መሰረት መሬት ለመቆፈር የወጡት ለመታየት ብቻ አልነበረም። ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ እንደጻፉት አንድ ቀን ምኒልክ ከመኳንቶቻቸው ጋር የየካን ዱር ሲመነጥሩ ጋሬጣና እሾህ እግራቸውን እየቀደደ ደም ብቻ አደረገው። በዚያ የነበሩ መኳንንትም ከምኒልክ እግር ብዙ ደም ሲፈስ አይተው ተደናገጡ። ወዲያውም በየሻማቸው የምኒልክን ደም ለመጥረግ ሲሻሙ ምኒልክ ተቆጥተው ተው አትንኩኝ ይልቅስ እኔ ለእናንተ ምሳሌ እንደሆንኩ፣ እናንተም ለበታቾቻችሁ ላለው ሰው አሳዩ፣ አስተምሩ ከዚያ ወዲያ ትርፉንና ጥቅሙን ታዩታላችሁ አሏቸው። ይህንን ካሏቸው በኋላ መኳንንቱ ሁሉ ዶማና መጥረቢያውን እየያዙ ዱሩን መመንጠር ጀመሩ።

ምኒልክም ታታሪነትንና ሥራ አክባሪነትን በዘመኑ ለነበሩት ሕዝባቸውና መኳንቶቻቸው አስተማሩ። በዚህም ሁኔታ የረሃቡ ዘመን ተፈፅሞ የተድላና የጥጋብ ዘመን ተጀመረ። ያ ክፉ የረሃብ ዘመን አልፎ ሰብል መታየት ሲጀምር ሕዝቡ:-

እህል ዱር አደረ ብቻውንም ዋለ፣
ጠላት እንደሌላው ሰው እንዳልገደለ።
እህል ዘሞቶ ገባ እኛም አየነው፣
አያሌ ሰው ቀረ ሳይገናኘው። እያለ
ይቀኝ ጀመር።

ዛሬ ሃገራችን ኢትዮጵያ ረሃብ ሌላኛው መታወቂያዋ ከሆነ ሰነባብቷል፣ በተደጋጋሚ ረሃብ ያስከተለብን ሰቆቃ የብዙዎቻችንን አንገት አስደፍቷል፣ እናቶችንና ህፃናትን እንባ አራጭቷል፣ አንዳንዶቹም ኢትዮጵያዊ ነን ለማለት እስኪያፍሩ ድረስ ረሃብ የደመቀና የረዥም ጊዜ ታሪካችን ላይ ጥቁር ጠባሳ ጥሎብናል። ይሄን ለዘመናት እንደ መዥገር ተጣብቆብን ቁም ስቅል እያሳየን ያለውን ረሃብ ለማስወገድ ከልብ በንሰሐ ከእግዝአብሔር ታርቀን፣ ስንፍናን ከእኛ በማራቅ ለሥራ በመትጋት የንጉሱን የአፄ ምኒልክን አሠረ ፍት ልንከተል ይገባናል። ቅድስት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከማንም በላይ ስለ ሥራ ክቡርነት በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም አስተምራናለች።

የቤተክርስቲያናችን መመሪያ የሆነው ቅዱስ መጽሐፍም:- «ሊሰራ የማይወድ አይብላ» በማለት ይመክረናል። ስለዚህም የዛሬው ትውልድ የእድገት መሠረቱ ሥራ ነውና የሥራ ክቡርነትን ተገንዝቦ በድህነት ለምትማቅቅ ሃገራችን ተግቶ ሊሰራ ይገባዋል። ቤተ ክርስቲያናችንም ሰው ሁሉ ከእጁና ከላቡ ፍሬ ይብላ ዘንድ ታዘናለችና።

## የውጫሌ ውል፣ የአድዋ ጦርነትና እቴጌ ጣይቱ

እቴጌ ጣይቱም:-....በውጫሌ የተዋዋልንበት ወረቀትም ቢሆን ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ውስጥ ታድራለች የሚል ቃል ታማርኛው አይገኝበትም እንዲህ ያለ ቃል ተጽፎበታል የምትል እንደሆነ ተሆነልህ አሳየን። በትላንትናውም ነገር የሆነ እንደሆነ አንተው ወደህ የአስራሰባተኛው አንቀፅ ክፍል ነገር አይነሳ ብትል ይኸው ተጣፈ። አሁን ለምን ነው መጠጠትህ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ድረስ ጃንሆይ ከተናገሩት ሁሉ አንድም ቃል አልተዛባም፣አል ተዛነፈም ብለው ተናገሩት።



www.ethiopianorthodox.org

አንቶኔሊም ውጫሌ የተዋዋልንበት ወረቀት በፈረንሣይ ቋንቋ የተጣፈው ይታይልኝ ብሎ አመለ ከተ:: እቴጌ ጣይቱም እኛ የምና ውቀው በአማርኛ የተጣፈውን ነው እንጂ የፈረንጅኛ ቋንቋ አናውቅም፤ አንተ ግን የእኛን ቋንቋ ታውቃለህና በአማርኛ የተጣፈውን እየው አሉት:: ከዚህ በኋላ ኮንት አንቶኔሊ ተናዶ ያን ትናንት የተጣፈውን ወረቀት ቀዳዶ ጥሎ ውሉን የኢጣሊያ መንግሥት በጦር ኂይል እንደሚያስከብር ተናገረ:: ይህን የሰሙት እቴጌ ጣይቱም ስቀው የዛሬ ሣምንት አድርገው በዚህ የሚደነግጥልህ የለም ሂድ የፎከርክበትን አድርግ እኛም የመጣውን እንመልሰዋለን:: እግሩን ለጠጠር፣ ደረቱን ለጦር ሰጥቶ አገሩን የማያድን ሰው በዚህ የሌለ እንዳይመስልህ የገዛ ደሙን ገብሮ ለገዛ አገር መሞት ጌጥ ነው እንጂ ሞት አይባልም፣ አሁንም ሂድ አይምሽብህ የፎከርክበትን በፈቀድህ ጊዜ አድርገው እኛም ከዚህ እንቆይሃለን አሉት::

ኢጣለያዊ ፀሐፊ ሳሊምቢኒ በጻፈው ማስታወሻው አንቶኔሊ የውሉን ማሻሻያ ቀዳዶ በጣለው ጊዜ እቴጌ ጣይቱ:- እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከመቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ ብለው መናገራቸውን በማስታወሻው አስፍሯል::

በውጫሌ ውል አንቀፅ 17 ምክንያት አፄ ምኒልክ ባለ መስማማታቸው ኢትዮጵያና ኢጣሊያ ወደ ጦርነት ገቡ:: አፄ ምኒልክም ህዝባቸውን ለማዝመት ቀጥሎ ያለውን ክተት አዋጅ አወጁ::

*እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላትን አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ:: እኔም እስከአሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ስለ እኔ ሞት አላዝንም፣ ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም እንግዲህም ያሣፍረኛል ብዬ አልጠራጠርም:: አሁንም አገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአሔር የወሰነልንን የባሕር በር አልፎ መጥቷልና እኔም ያገሬ ከብት ማለቁንና የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር::*

*አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳለፌ አልሰጠውም ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም አንተም እስካሁን አላስቀየምኸኝም:: ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ:: ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በሐዘን እርዳኝ:: ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ:: አልተውህም ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም ዘመቻዬ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከትህ ላግኝህ::*

አጤ ምኒልክ መኳንንቱን ሰብስበው አንፍራ::እኔ እንደሆንሁ መዝመቴን አልተውምና ስለ ኢጣሊያ ዘመናዊ መሣሪያና ገናናነት አትንገሩኝ:: ኃይል የእግዝአብሔር ነውና የእናት አገሬን ጠላት እጋጠማለሁ:: ብትዘምትሙ ብትቀሩም ሬሳዬን ከጦር ሜዳ ፈልጉት በማለት ምኒልክ በባለቤታቸው የጦር ምህንድስና ምክር እና በእግዚአብሔር ኃይል ጠላታቸውን ድል አድርገው መላውን ነጭ ህዝብ ሁሉ የኃፍረት ካባ እንዲከናነብ አደረጉት፣ ድሉ ለጥቁር ህዝቦች የነፃነት ትግል ትልቅ ፋና ወጊ ሆነ::

*«በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ:: እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የእነዚያን ሁሉ ክርስቲያን ደም በከንቱ መፍሰሱን እያየሁ ድል አደረግኋቸው ብዬ ደስ አይለኝም»* በማለት ምኒልክ ለአወሮፖዊው የዲኘሎማት ለሙሴ ሽፍኔ በመጋቢት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በፃፉለት ደብዳቢያቸው ገልፀውለታል::

*«ሃያሺህ ያህል ወታደሮች ያለበት የአውሮፖ ጦር በአፍሪካ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ተሸነፈ:: በእኔ እምነት መሰረት በዘመናችን ታሪክ ውስጥ እንደ አድዋ ያለ ጦርነት የለም በእልቂቱ 25,000 ሰዎች በአንድ ቀን ጀምበር የሞቱበትና የቆሰሉበት ነበር:: ፖለቲካና ታሪክ አበቃ በአፍሪካ ውስጥ ታላቅ የተወላጆች ኃይል መነሳቱ ታወቀ:: የአፍሪካ ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ተለወጠ:: ጥቁር ዓለም በአውሮፖውያን ላይ ሲያምፅና ሲያሸንፍ የመጀመሪያው መሆኑ ነው:: አበሾች ጠቢባን ብልህና ጀግና ሕዝቦች መሆናቸው ከአራት ዘፈጥረት ጀምሮ ተፅፎላቸዋል:: የእኛም ዓለም ገና ቶር እና ኦዲዩን በሚባሉ አማልክት ሲያመልክ በነበረበት ጊዜ አበሾች የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበሉ ሕዝቦች ናቸው:: የነጮችን የቅኝ ግዛት መስፋፋትና ቅዠት፣ የኃያላኑን አገሮች ፍላጐት አድዋ ዘጋው::»*

በማለት በርክሌይ የተባለው አውሮፖዊ ፀሐፊ የኢትዮጵያዊያንን የእምነት ጥንካሬና ጀግንነት ስለአደዋ ውሎ በጻፈው ማስታወሻው ላይ አስፍሮታል::

*«የተተከለው ድንኳን ሲታይ ከብዛቱ የተነሳ አፍሪካ ኤሮፖን ለመጠራረግ የተነሳች ይመስላል:: የጦርነቱ እለት ኢትዮጵያዊያኑ ዳማቅ ቀለም ያለው ካባ ለብሰው፣ ጠመንጃንና ጦር ይዘው፣ ጐራዴ ታጥቀው፣ የነብርና ያንባሳ ቆዳ ለብሰው አዝማሪዎቹ እያቅራሩና እየፎከሩ ቄሶች፣ ሴቶች፣ ልጆች ሳይቀሩ ፀሐይዋ ፈንጠቅ ስትል በተራራው ላይ በታዩ ጊዜ የኢጣሊያን ጦር አሸበሩት»*...በማለት በርክሌይ የታዘበውን አስፍሯል::

ለአገራቸው ነፃነትና እድገት ሌት ተቀን ሲለፉ የነበሩት የአፄ ምኒልክ ሞት በተሰማ ጊዜ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ህፃን አዋቂ ሳይል እጅግ በሐዘን ተዋጠ፣በሐዘን አንጉርጉሮውም እንዲህ ሲል «እምዬ» ለሚላቸው ንጉሡ ሙሾ አወረደ:-

*ቀድሞ የምናየው የለመድነው ቀርቶ፣*
*አንግዳ ሞት አየሁ አባቴ ቤት ገብቶ::*
*ምልክቱ ይህ ነው፣የንጉሥ ሞት ሐዘን፣*
*<u>ጣይቱ</u> ስተጨልም ጨረቃ ደም ስትሆን፡*
*እጅግ አዝኛለሁ አልቅሳብኝ አገሬ፣*
*የሁሉ አባት ሞቶ ተጐዳችሁ ዛሬ::*
*አጤ ምኒልክ ንጉሡ*
*ኣባ ማቴዎስ ጳጳሱ*
*ቃኘው መኮንን ራሱ*
*ሄዱ ይላሉ ገሥግሡ*
*አምብዛም አሽከር አልቀራቸው*
*ሁሉም ተከተሏቸው::*
*ያ ዳኘው ምኒልክ ሁዳዱን አሰፍቶ፣*
*በየቦታው ተልሞ በየቦታው ተግቶ*
*ሳይጨርስ አረፈ አዝመራውን ትቶ::*

*(ከባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱና ከሕዝቡ የተገጠመ)*

# የእንጦጦ ራጉኤልን ታሪካዊ ቅርሶች ለማዳን ምእመናን ከፍተኛ ርብርብ እያደረጉ ነው



ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው ጥንታዊ የብራና መጸሐፍት ጥቂቱ

የእንጦጦ የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል የ125 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ቤተክርስቲያን ነው:: በነዚህ ረዥም ዓመታት ውስጥ ቤተክረስቲያኑ ያከማቻቸው ቅርሶች በረካታዎች ናቸው:: የቀደሙት ነገሥታት ቅርሶቻቸውንና ውድዋጋ ያላቸውን ሀብቶቻቸውን ያስቀምጡ የነበረው በአብያተክርስቲያናት ውስጥ በመሆኑ፣ ይህም ጥንታዊ ቤተክርስቲያን የአፄ ዮሐንስ፣ የዳግማዊ አፄ ምኒልክ፣ የእቴጌ ጣይቱና በዘመኑ የነበሩ የታላላቅ መንፈሳውያን አባቶችና እናቶች የቅርስና የታሪክ ማኅደር ሆኖ ኖሯል:: ከእነዚህም ብርቅዬ ቅርሶች መካከል አያሌ ዘመናትን ያስቆጠሩ የብራና መጽሐፍት፣ አልባሳት፣ ንዋየ ቅድሳት፣ መንፈሳዊ ስዕሎች፣ አፄ ዮሐንስ ወደ መተማ ይዘውት የዘመቱት ድንኳንና ልዩ ልዩ መንፈሣዊ አገልግሎት የሚካሄድባቸው ቁሳቁሶች ወዘተ...ይገኙባቸዋል::

የተጠቀሱት ቅርሶች በሥርዓት ተጠብቀው ባለመቀመጣቸውና እንደማንኛውም ተራ ንብረት በዕቃ ቤት ውስጥ ያለአንዳች እንክብካቤ ሲንገላቱ በመቆየታቸው ለከፍተኛ ብልሽትና ጉዳት ሊጋለጡ ችለዋል:: ከእነዚህ እጅግ በጣም ከባድ ጉዳት ከደረሰባቸው ቅርሶች መካከል በተለይ ጥንታዊ የሆኑ የብራና መጻሕፍትና አልባሳት ያሉበትን አደገኛ ሁኔታ የኢትዮጵያ ቴሊቪዥን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በማስተላለፉ ብዙዎች ቁጭታቸውንና ሀዘናቸውን በእንባ ጭምር ሲገልጹ ቆይተዋል:: በመሆኑም እነዚህን ቅርሶች ከውድመት ለማዳን በደብሩ አስተዳዳሪና በሰበካ ጉባዔ አባላት አስተባባሪነት ተቆርቋሪ፣ ሀገር ወዳድ ምዕመናን የተሰባሰቡበት አንድ የልማት ኮሚቴ በአስቸኳይ ተቋቁሞ ከሐምሌ ወር 1996 ዓ.ም ጀምሮ እነዚህ ብርቅዬ፣ ውድና የኢትዮጵያዊነታችን መገለጫ የሆኑት ቅርሶቻችን ቋሚ ሥፍራ አግኝተው ለጉብኚዎች የሚታዩበትን አንድ ዘመናዊ ሙዚያም ለማሰራት የእርዳታ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ ጀምሯል:: በዚህም መሰረት በመንበረ ልኡል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በተደረጉት በርካታ ስብሰባዎች፣ ስለቅርሶቹ ሁኔታ በአጠቃላይም ስለእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ታሪካዊነትና ስላሉበት ችግሮች ገለፃና ውይይት በማካሄድ ለሀገራቸው ቅርሶችና ለቤተክርስቲያናቸው መጠበቅ አበክረው ከሚያስቡና ከሚቆረቆሩ ወገኖች ከብር 10,000 እስከ 1 ብር ድርስ ተበርክቷል፣ ለወደፊቱም የርዳታው አሰባሰብ በዚሁ መሠረት ይቀጥላል::

በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሊሰራ የታሰበው ሙዚየም ደረጃውን የጠበቀ ከቦታው ታሪካዊነት ጋር አብሮ ሊሄድ በሚችል አኳኋን ንድፉ ተዘጋጅቶ ያለቀ ሲሆን ለግንባታ ሥራው ከአራት ሚሊዮን ብር በላይ (4,000,000 ብር) እንደሚጠይቅ ተገምቷል:: የሙዚየሙ ንድፍ በነፃ የተዘጋጀው የቅርሶቹን ሁኔታ አይተው ከፍተኛ ሐዘን በተሰማቸውና የቦታውን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት በሚያውቁ ጀርመናውያን የምህንድስና ባለሙያዎች ሲሆን፣ እነዚህ ታሪክ አፍቃሪ ባእዳን የሀገራችን ዜጐች ሳይሆኑ በቅርሶቹ ላይ እያደረሰ ያለው ብልሽትና ውድመት አስቆጭቷቸው በበጐ ፈቃደኝነት በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ድንኳን ተክለው ጥናት በማድረግ ዲዛይኑን ያለምንም ክፍያ በራሳቸው ተነሳሽነት ማዘጋጀታቸው ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነና በቀዳሚነትም የቅርሶቹ ባለቤቶች የሆነውን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ስሜት የሚነካና ለበጐ ሥራ የሚያነሳሳን እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም::

በዚሁም መሠረት ለእነዚሁ ቅርሶች መጠበቂያ የሚሆነውን ይህንን ሙዚያም ለማሰራትና ቤተክርስቲያኑም ኢትዮጵያ ሀገራችን ከምትኮራባቸው ድንቅ ሥራዎች መካከል አንዱ በመ



www.ethiopianorthodox.org



የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚቴ አባላት በከፊል




ጥንታዊ አልባሳትና አክሊሎች

ሆኑ ተንከባክቦ ለትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል የልማት አስተባባሪ ኮሚቴው ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን በሥሩ በማዋቀር ስታቀደው ሥራ ማስፈፀሚያ የሚሆነውን ገቢ በተጠናከረ ሁኔታ በማሰባሰብ ላይ ነው:: የልማት ኮሚቴው ለያዘው እቅድ ተፈፃሚነት ከነደፋቸው መርሀ ግብሮች መካከል የመጀመሪያው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የቤተክርስቲያኑን ታሪካዊነትና የቅርሶቹን መገኘት በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በማስተዋወቅ ድጋፍ የሚገኝባቸውን አውታሮች መዘርጋት ነው:: ይህንንም እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በተለያዩ የዜና ማስራጫዎች ችግሩ በሕዝቡ ዘንድ እንዲታወቅ ጥረት እያደረገ ከመ ሆኑም ሌላ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ በመከበር ላይ የሚገኘውን የቤተክርስቲያኑን 125ኛ ዓመት በአል ምክንያት በማድረግ የእርዳታ ማሰባሰቢያ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን እያካሄደ ነው:: እነዚህና በሌሎችም በተከታታይ በሚካሄዱ መንፈሳዊ መርሀ ግብሮች አማካኝነት በሚገኘው ገቢ የሙዚየሙ ግንባታ ሥራ ይካሄዳል:: ሙዚየሙ በሀገሪቱ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ሙዚየሞች አንዱ ስለሚሆን ለዚሁ ዓላማ ግብ መምታት የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ አስተዋጽኦና ርብርብ ይጠይቃል:: ሃይማኖትን፣ ባህልን፣ ቅርስና ታሪክን በመጠበቅ ረገድ የኢትዮጵያ ህዝብ በየዘመናቱ የፈፀማቸው ተግባሮች የሚደነቁ ናቸው:: በአሁኑ ወቅት አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ ለመጪው ትውልድ ቅርስ ሆነው የሚኖሩ ታላላቅ ስራዎች እያከናወነ ነው:: ታሪክ፣ ቅርስና ሃይማኖት ተነጣጥለው የማይታዩ የትውልድ መታወቂያዎች እንደ መሆናቸው ምእመናኑን የቅዱስ ራጉኤልን ሙዚየም በመገንባት ለትውልድ መኩሪያ የሚሆን ሐውልት እንደሚያቆም ጥርጣሬ የለንም::

⌖ ⌖ ⌖

www.ethiopianorthodox.org

# የእንጦጦ ራጉኤል አመሠራረተ ታሪክ



የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን

የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ህንጻ መሠረቱ የተጣለበትና ሥራው ተጠናቆ ታቦቱ ወደ መቅደሱ የገባበትን ዓመተ ምህረት የተለያዩ የታሪክ ጸሐፍት የተለያዩ መረጃዎችን ጽፈዋል፤ በፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ረቂቁ ተጻፈ በተባለውና በእነ ሊቀ ሊቃውንት ኃይለ መስቀል ገብረመድህን ተሰባስቦና ተጠናቅሮ ለህትመት በበቃው "<u>ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒሊክ</u>" በተባለው መጽሐፍ ውስጥ የቤተ ክርስቲያኑ ህንጻ መሠረቱ የተጣለው በ1877 ዓ.ም ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑ ተሠርቶ ታቦቱ ወደ መቅደሱ የገባው በ1882 ዓ.ም እንደነበር ተጠቅሷል።

አለቃ ዓይናለም ገብረ ማርያም ዘራጉኤል የተባሉ ታሪክ ፀሐፊና ጋዜጠኛ በመጽሐፋቸው የሐዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን በ1872 ዓ.ም መሠረቱ ተባርኮ ሥራው ተጠናቆ ታቦቱ ወደ መቅደሱ የገባው በ1877 ዓ.ም እንደነበር ጽፈዋል፣ የእኝሁ ፀሐፊ መረጃ በ1945 ዓ.ም በታተመው የቀን መቁጠሪያና አጀንዳ ላይ ተረጋግጦ ተጽፏል።

በዚህ መረጃ መሠረት ቤተ ክርስቲያኑ መሠረቱ ከተጣለበት ጊዜ ጀምሮ 125 ዓመት እንደ ሆነው ያመለክታል። በእነዚሁ ረጅም ዓመታት ውስጥ ቤተ ክርስቲያኑ የተጓዘበትን የታሪክ ሂደት ለማጤን በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል፤ እነዚህም ከ1872-1948 ዓ.ም የነበሩትን ዘመናትና ከ1948 እስከ አሁን ድረስ ያሉትን ዓመታት ያካትታል።

ከ1872 - 1948 ዓ.ም ድረስ የነበሩት ዘመናት በዚህ ቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ወርቃማ ዘመን ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ ሲሆን ከ1948 ወዲህ ያሉት ዓመታት የችግር፣ የጉስቁልና፣ የእርዛት በአጠቃላይም ቤተክርስቲያኑ የጥንት ማዕረጉንና ክብሩን ተገፎ ጨርሶ የተረሳበትና በድህነት አዘቅት ውስጥ የወደቀበት ዓመታት ናቸው።

የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ወርቃማ ዘመን ታሪክ ከአመሠራረቱ የሚጀምር ሲሆን የህንጻ ግንባታው ሥራ በቤተ መንግሥቱ በተለይም በንጉሡ በአፄ ምኒሊክ ልዩ ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ ከዚያን በፊት ታይቶ በማይታወቅ የሥነ-ህንጻ ጥበብ በውጭ ዓዋቂች ሙያዊ እገዛ የተሠራ መሆኑ ነው። ፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ይህንኑ በማረጋገጥ "ከዚህ ቀደም እንዲህ ያለ ማለፊያ ሥራ ተሠርቶ አላየንም" ሲሉ አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ሲሰራ ድንጋዩ ለኖራ እንዲስማማ አራት ማዕዘን እየሆነ እየተጠረበ ንጉሡም ራሳቸው እየጠረቡ እንጨቱ በሠረገላ ከመናገሻ እየመጣ ቅኔ ማህሌቱም፣ ቅድስቱም፣ መቅደሱም ስምንት ስምንት ማዕዘን ሆኖ ተሠራ። አፄ ምኒሊክ የእጅ ሥራ ዝንባሌ ስለነበራቸው በአብዛኛው ስራውን የሚመሩት እርሳቸው ነበሩ። ቤተክርስቲያኑ የሚሰራው በጥርብ ድንጋይ ስለነበረ ድንጋዩ በመንኰራኩር እየተጋዘ ሲቀርብ እየጠረቡ ለሠራተኞች የሚያሣዩት ራሳቸው አፄ ምኒሊክ እንደ ነበሩ የግንባታው ሥራ ታሪክ ያመለክታል።



www.ethiopianorthodox.org

ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ በዘመነ
መንግሥታቸው ለሀገሪቱ ሥልጣኔና
ዕድገት መሠረት የሆኑ የተለያዩ
ተቋማትን በመገንባት ፋና ወጊ
እንደ መሆናቸው ሁሉ ሕዝቡ ለሀ
ይማኖቱ ጽኑና ፈሪሀ እግዚአብሔር
እንዲያድርበት በርካታ ገዳማትንና አ
ድባራትን ሠርተዋል። ከእነዚህም
አብዛኛዎቹ በግራኝ መሀመድ ወረራ
ወቅት የተቃጠሉና መልሰው የተገነ
ቡ ነበሩ። የቅዱስ ራጉኤል ቤተ
ክርስቲያን ግን ከአበው በተነገራቸው
ትንቢት መሠረት በእርሳቸው የተ
መሠረተ ቤተ ክርስቲያን ነው።
ዳግማዊ አጤ ምኒሊክ ጠባቂያቸው
ለሆነው ለእንጦጦ ራጉኤል ቤተ
ክርስቲያን ሥራ ልዩ ትኩረት መስ
ጠታቸውን ከሚያመለክቱት አንዱ
ህንጻው በልዩ የኪነ ህንጻ ጥበብ
በጊዜያዊነት ሳይሆን ዘላቂ በሆነ
አኳኋን እንዲሠራ ማድረጋ
ቸው ነው።

በዘመናቸው በእንጦጦ ተሠር-
ተው የነበሩት አብያተ ክርስትያናት
ሁሉ በጭቃ ግንብና በሣር ክዳን
የተሠሩ ስለነበር ሁሉም ፈርሰው
በንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱ እንደ
ገና መሠራታቸውን ደጃዝማች ከበደ
ተሰማ "የታሪክ ማስታወሻ" በተባ
ለው መጽሐፋቸው ጽፈዋል። የእን
ጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ግን
በጊዜ ሂደት አንዳንድ አነስተኛ ማሻ
ሻያዎች ከመደረጋቸው በስተቀር
እስከ ዛሬ ያለው ህንጻ የዳግማዊ
ምኒሊክ ሥራ ነው ።

የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል
ቤተክርስቲያን ሥራ አዳዲስ ቴክኖ
ሎጂዎች በሀገሪቱ ውስጥ እንዲ
ለመዱ ፈር ቀዳጅ መሆኑንም አንዳ
ንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቀድሞ
በኢትዮጵያ ተለምዶ የነበረው የቤተ
ክርስቲያን አሠራር ክብ ሲሆን
በቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያ አሠ
ራር ግን ስምንት ማዕዘን ሆኖ ፎቅ
እንዲሆን መደረጉ ንጉሡ ጠባቂ
ያቸው ለሆነው መልአክ ልዩ ነገር
ለመሥራት እንዳሰቡ ያመለክታል።
በቤተክርስቲያኑ የህንጻ ግንባታ
ውስጥ ከሀገር ውስጥ ታዋቂ ግንበኞ
ች ከአንኮበርና ከጐንደር እንዲመጡ
አድርገዋል፤ እንዲሁም ከውጭ ሰዎ
ች አንኮበር ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ
ከምኒሊክ ቤተ መንግሥት ተለይቶ
የማያውቀውን የህንድ ተወላጅ ሀጂ
ካዋስ ምርጥ ባለሞያ በመሆኑ በዚህ
የህንጽ ሥራ ውስጥ ግንባር ቀደም
ተሣታፊ አድርገውታል።

በ1877 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ
የመጡ ሦስት የስዊዝ ጥበበኞች
በዚሁ ቤተክርስቲያን የግንባታ
ሥራ ውስጥ በማሣተፍ የአው
ሮፓን የህንጻ ግንባታ ቴክኖሎጂ
እንዲያካፈሉ ተደርጓል። ምኒሊክ
ሀጂ ካዋስን ወደ ኤደን በመላክ
ከየመን ባለሙያዎችን እንዳ
ያስመጣ በማድረግ በህንጻ ግንባ
ታው ሥራ ተሣታፊ እንዲሆኑ አ
ድርገዋል። ማየር የተባሉ የጀ
ርመን ሚሲዮናዊ በተለይ በበሬ
የሚሳቡ መንኮራኩሮችን እንዲ
ሠሩላቸው በማድረግ ከአካባቢው
ድንጋይና ከመናገሻ ግንድ ለማጓ
ጓዝ ተጠቅመውበታል፣ ዱብዩስ
የተባለ ፈረንሣዊ በመናገሻ የደን
ኃላፊ አድርገው በመመደብ ግን
ዱን በልክ በልኩ እያስቆረጠ
በመላክ ሥራው እንዲፋጠንና
ዘመናዊ አሠራር እንዲኖረውም
አድርገዋል።

አቶ ሀብተ ወልድ ወልደ
ሃና ዋና የብረት ቀጥቃጭና አንጥ
ረኛ ነበሩ። እርሳቸው ምስማር
ማጠፊያዎችንና መወርወሪያዎችን
በማቅረብ የታወቁ ባለሙያ እን
ደነበሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ በመ
ጽሐፋቸው እኝህን ባለሙያ ስራ
ቸው ከፋብሪካ የማይተናነስ ነው
በማለት አድንቀዋቸዋል።

አፄ ምኒሊክ በዚህ ቤተ
ክርስቲያን ሥራ ውስጥ ኢትዮጵያ
ውያን ሙያ እንዲቀስሙ ከማ
ስቻላቸውም ሌላ የተለያዩ የህብረ
ተሰብ ክፍሎችን በማደራጀት
በቤተክርስቲያኑ ግንባታ ውስጥ
እንዲሣተፉ አድርገዋል። በወቅቱ
ከነበሩት የሥራ አደረጃጀቶች
መካከል የድንጋይ ፈላጭ ቡድ
ን ነበር፤ ቡድኑ በዓመት ሁለት
ወር በድንጋይ ፈላጭነት የሚሠራ
ሲሆን በጉልበት ያደረገው
ተሣትፎ በግብር መልክ ታሳቢ
ይሆንለት ነበር። በቤተክርስትያኑ
ሥራ ገባሮች፤ እስረኞችና ሌሎ
ችም በጉ ፈቃደኞች ተሣታፊ
ሆነዋል።

ቤተ ክርስቲያኑን ለመ
ሥራት ከመናገሻ የሚጓጓዘው ግን
ድ እንጦጦ እስከ ሚራገፍበት ድ
ረስ ሦስት ቀናት ይፈጅ ነበር፤
አንዱን ግንድ ለመሸከም 12 ሰው
ሲመደብ ሥራው አድካሚ በመ
ሆኑ በየቦታው የግብር ቤት
ተዘጋጅቶ እየተመገበ ያጓጉዝ ነ
በር። ከእነዚህም ግብር ቤቶች
ዋንኛው ሥጋ ሜዳ ላይ የተሠራው
ሲሆን በዚህ ሥፍራ ሠራተኛው
ፍሪዳ ተጥሎ እንደልብ እየበላ የደ
ከመ ጉልበቱን የሚያበረታበት ነ
በር። ንጉሡም እየተጓጓዙ ተሸካ
ሚውን በማበረታታት ሥራው እን
ዲቃና ከፍተኛ አስተዋጽ ነበ
ራቸው።


ቱርክ ባሻ ታምሬ የቤተ
ክርስቲያኑ የግንባታ ሥራ የቅርብ
ተቆጣጣሪና ለንጉሡ ሪፖርት አሓ
ራቢ ነበሩ። እኝህ ሰው በምኒሊክ
ጦር ውስጥ የጀነራልነት ማዕረግ የነ
በራቸው በጀግና ተዋጊነታቸው
የታወቁ ስለነበሩ ቱርክ ባሻ
የተባለውን ማዕረግ ያገኙትም በጦር
መሪነታቸው ነበር፣ አዛዥ ወልደ
ጊዮርጊስ ደግሞ የግንበኞች
አለቃ ነበሩ።

የቤተክርስቲያኑ የጣሪያው
ክዳን መጀመሪያ የመጣው ከግ
ብጽ ነበር፣ በወቅቱ ይህ ክዳን
"የኢየሩሳሌም ድንጋይ" እየተባለ
ይጠራ የነበረ ሲሆን ይዘቱ የአስ
ቤስቶስ ሸክላ ነው። ጣሪያው በኋላ
ወደ ቆርቆሮ ሲቀየር ከፈረንሣይ
በመጣ ቆርቆሮ እንዲከደን ተደረገ፣
ይኸንንም ሥራ ተከታትለው እንዲ
ያስፈጽሙ የተሾሙት ፊታውራሪ
ኢብሳ ነበሩ። የቤተክርስቲያኑ ጣ
ሪያ ለሦስተኛ ጊዜ በንግሥተ ነገ
ስታት ዘውዲቱ ተሻሽሎ እንዲሰራ
የተደረገ ሲሆን ዕድሞውንም በግ
ሪክ ባለሙያ ያስገነቡት ንግስቲቱ
ናቸው። በአጠቃላይ የቅዱስ ራጉ
ኤል ቤተክርስቲያን ህንጻ ሥራ
አዳዲስ ቴክኖሎዎጂ የታየበት፣ በር
ካታ ባለሙያዎች፣ የተሳተፉበት
በብዙ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ
የተባበረበት የአፄ ሚኒሊክ የመጀ
መሪያው ትልቁ ሥራቸው ነበር።

የቤተክርስቲያኑን የውስጥ ግ
ድግዳ ስዕሎች ከሳሉት ታዋቂ የጊ
ዜው ሰዓሊያን መካከል አለቃ ዘዮ
ሐንስ አንዱ ነበሩ። እርሳቸውም
የመጡት ከማህደረ ማርያም ደብረ
ታቦር ሲሆን በሙያቸው አፄ
ዮሐንስንና አፄ ሚኒሊክን አገልግ
ለዋል፤ ስዕል ቤት ኪዳነ ምህረ
ትንም የሳሉ እርሣቸው ነበሩ።

ሌላው ታዋቂ ሰዓሊ አለቃ
ሉቃስ ነበሩ፣ እርሳቸውም ከጉጃም
የመጡ ሰዓሊ ሲሆኑ ከእንጦጦ ራጉ
ኤል ሌላ አድዋ ሥላሴን፣ አዲስ
አለም ማርያምን፣ የካ ሚካኤልንና
የደብረሊባኖስን ገዳም ስዕሎች የሳ
ሉ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org



*ቅዱስ ራጉኤል ለዳግማዊ ምኒልክ በትረ መንግሥቱን ሲያስረክባቸው*

አለቃ ማህሉ በሰዓሊነት ተማታፊ ከነበሩት መካከል አንዱ ነበሩ፣ አለቃ ማህሉ የአለቃ ሉቃስ ልጅ ሲሆኑ እርሳቸው የአዲስ አበባን ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያንን ስዕሎች በመሳልም ተሳታፊ ነበሩ።

አለቃ ኤልያስና አለቃ መዝሙር ዘዳዊትም በስዕሉ ሥራ ላይ ተሳትፈዋል፣ ከአውሮፓ በስዕል ሙያ ሰልጥነው የተመለሱት አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስም ከሙያቸው ቱራፋት አካፍለዋል። እነዚህ ባለሙያዎች በሰሯቸው የሥዕል ሥራዎች በወቅቱ በርካታ የውጪ ሰዎች ተደንቀዋል። ከነ ዚህም መካከል ቪቫን፣ ፓዌል ኮተንና ዶክተር መረብ የተባሉ የውጪ ተጓገሮች ይገኙበታል።

ግሊቾን የተባለው ተጓዥ በ1890 ዓ.ም በሚኒሊክ ግብግር በራጉኤል ንግስ ላይ መገኘቱን ገልጾ በዓሉ እጅግ በጣም ደማቅና ማራኪ፣ ትዝታው ምንጊዜም የማይጠፋ እንደነበር ጽፏል። ፓውል ኮተን የተባለው ተጓዥ ደግሞ "በአቢሲንያ ምድር እንዲህ ዓ ይነት ቤተክርስቲያን አልታየም ቁመቱና ግዝፈቱ አራት ፎቅ ያክላል"።

ምኒሊክ መስከረም 1 እና ግንቦት 1 ቀን በዓለ ንግሱን ያከብሩ ነበር። አዲስ አበባ ከወረዱም በኋላ ታቦቱን ማንገሳቸውን አላቋረጡም ነበር። ታቦቱ ሲወጣና ዐ -ደት ሲያደርግ 12 ጊዜ መድፍ ይተኮሳል። የጠመንጃ ተኩሱ እጅግ የተጧጧፈ ነበር፣ ምኒሊክ በከፍተኛ አጀብ በቤተክርስቲያኑ ይገኛሉ፣ የእንግሊዝ ዲፕሎማቶችም በበዓሉ ሥፍራ ላይ ይገኙ ነበር። 15000 ያህል ወታደሮች ይሰለፉሉ፣ ንጉሡ ከመቀመጫቸው ተነስተው ጠመንጃቸውን አንግተው 3 ጊዜ በዝግታ ቤተክርስቲያኑን ከታቦቱ ጋር ዑደት ሲያደርጉ የጠመንጃ ተኩ ሱ ይቀልጣል፣ የእንግሊዝ ንግስት ልጅ በወለዱ ዕለት የሚደረገውን ያህል የደመቀና የሞቀ በእጅጉ ሐ ሴት የሚንጸባረቅበት መንፈሳዊ ሥርዓት እንደሆነ በዝርዝር ጽፏል።

ለመሆኑ አፄ ምኒሊክ ህንጻ ቤተክርስቲያኑን ካሰሩ በኋላ የቅዱስ ራጉኤልን ጽላት ለማስገባት ለምን መረጡ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መላ ኢትዮጵያ በግራኝ መሀመድ ወረራ በሚታመስበት ወቅት ንጉሡ አፄ ልብነ ድንግል በወረራው ሳቢያ ህዝባቸውና መንግሥታቸው በመናወጡ እርሳ ቸውም ከቦታ ወደ ቦታ ለመንከራተትና ለመሰደድ ተገደው ነበር። በአብያተ ክርስቲያናትም ላይ ከፍተኛ ቃጠሎና ዘረፋ ተካሂዶባቸዋል። በዚሁ ፈተናና ጭንቀት በመላ ሀገሪቱ ላይ ባጠላበት ወቅት ሊቀ መለእክት ቅዱስ ራጉኤል ለንጉሡ ለአፄ ልብነ ድንግል በራዕይ ተገልፆ "ልብነ ድንግልን አንተ በስደት ትሞታለህ፣ ከልጆችህም ውስጥ ገ ይንገሥ፣ (ገላውዲዎስ ይነግሣል)፣ ፊ ይመውት (ፊቅጦር ይሞታል) ሚ፣ ይስደድ (ሚናስ ይሸጣል(ያ ይኑበር) ያዕቆብ ይኖራል)" እያለ በንጉሡና በልጆቻቸው ላይ የሚደርሰውን ትንቢት እንደነገራቸው ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ "የግራኝ መሀመድ ወረራ



www.ethiopianorthodox.org

በሚለው" መጽሐፋቸው ገልጸዋል። ይህ የትንቢት ቃል በተግባር ተተርጉሞ ከመታየቱም በላይ በክብረ ነገሥት ላይ ተጽፎ እንደተገኘው ምኒልክ በቀድሙ አባቶቻቸው ከተማ ላይ የቅዱስ ራጉኤልን ቤተ ክርስቲያን ቢያሠሩ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ኢትዮጵያን አንድ አድርገው እንደሚያስተዳድሩ ለአፄ በተነገራቸው ቃል መሠረት ከ500 ዓመታት በኋላ እንጦጦን ፈልገውና አስፈልገው ለማግኘትና የራጉኤልን ቤተክርስቲያን ለማሠራት መነሻ ምክንያት ሊሆናቸው ችሏል።

አፄ ምኒሊክ ይህንን ቤተ ክርስቲያን ልዩ የፀሎት ቤታቸው በማድረግ መንግሥታቸውንና ሕዝባቸውን እንዲጠብቅላቸውና ኢትዮጵያን ታላቅ የማድረግ ምኞታቸውን እንዲያግኙላቸው ሲማፀኑት ኖረዋል፤ በመሆኑም ከዚሁ ቤተ ክርስቲያን ሥራ በኋላ ሲነገር የነበረው ትንቢት ተፈጽሞ በ1882 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታት በመሆን የሀገሪቱን መሪነት ጨብጠው ኢትዮጵያን አንድ በማድረግ እብሪት የመጣባቸውን ጠላት ሁሉ በድል አድራጊነት መልሰው ሀገራቸውና ሕዝባቸው ለጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የነፃነት አርአያ እንዲሆን አድርገዋል።

ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ በዘመነ መንግሥታቸው ላከናወኗቸው ታላላቅ ሥራዎች ሁሉ መሠረቱ የአባቶቻቸውን ቃልና ምክር እያዳመጡ መፈጸማቸው ነበር። በመሆኑም በዘመነ መንግሥታቸው ይህ ቤተክርስቲያን ከህንጻው አሠራር ጀምሮ ቀደምት እንዲሆን በብርቱ ጥረዋል፤ ቤተክርስቲያኑ ታላላቅ የተማሩና የተመራመሩ ሊቃውንት መፍለቂያ እንዲሆን ትኩረት ሰጥተው በዚሁ ደብር የታወቁ ሊቃውንትን እየመረጡ በተለያየ አገልግሎት ትክለኛ አድርገዋቸዋል። ከእነዚህም ውስጥ የአፄ ቴዎድሮስን የዘመን ታሪክ የጻፈው አለቃ ወልደ ማርያም ዘምሁይ ወንጌ ተጉለት በደብተራነት ተተክለው የደብሩ የመጀመሪያው ሊቀ ጠበብት ለመሆን በቅተዋል። የአፄ ምኒሊክ የመጀመሪያው የጽህፈት ሚኒስትር የነበሩት ፀሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ፣ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴና የመሳሰሉ ታላላቅ ምሁራንም የደብሩ የመጀመሪያዎቹ ትክለኞች ነበሩ።

ደብሩ የታወቁ ሊቃውንት መገኛ እንዲሆን ከመጀመሪያው ጠንካራ መሠረት የጣለለት በመሆኑ እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ ታላላቅ ምሁራንና አገርንና መንግሥትን በከፍተኛ ኃላፊነት በመምራት ግንባር ቀደም የሆኑ ትውልዶችን ለማፍራት አስችሏል። ከእነዚህም ታላላቅ ሰዎች መካከል ፀሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩ አቶ አካለ ወርቅ ሀብተ ወልድና አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ሚኒስትሮች የነበሩ፣ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሀዋርያት፣ አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

እንደ ዛሬው ሳይሆን እንጦጦ ራጉኤል ከራሱ ተርፎ ሃያ ሁለት የገጠር አብያተ ክርስቲያናት (ቅፊሮችን) በስሩ ያስተዳድር ነበር ከእነርሱም ለመጥቀስ ያህል ዳሎታ ሚካኤል፣ ፈንጨዋ ማርያም፣ ሂዲ ጊዮርጊስ፣ እንዶዴ ጊዮርጊስ፣ ጨንቆሌ ሚካኤል፣ በዲ ሥላሴ፣ ካም ጊዮርጊስ፣ ሴራ ሚካኤል፣ የቱፋ ሙና አገር ጊዮርጊስ፣ ላይ ጊዮርጊስ፣ የረር ሥላሴ፣ ቆቃ ገብረኤልና ሌሎችም ነበሩ።

እንጦጦ ራጉኤል ደብረ ኃይል የሚለውን ስያሜና የደብሩ አስተዳደሪ የማዕረግ ስም መልአከ ኃይል እንዲባል የፀደቀለትም በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ነው። የቤተክርስቲያኑን ሀብት እንዲጠብቁ ገበዞች የሚሾሙትም በራሳቸው በንጉሠ ነገሥቱ ሲሆን የቤተክርስቲያኑ የመጀመሪያ ገበዝ ራስ መኰንን ነበሩ። ቀጥሎም የወሎው ራስ ሚካኤል ተሹመዋል።

ደብረ ኃይል እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ የተሰጠው ክብርና ማዕረግ በዚህ ሁኔታ [illegible] ጀምሮ ያ ወርቃማ ዘመን ታሪኩ፣ አበባውና ፍሬው ረግፎ የታሪክ ሒደቱ እያዘቀዘቀ የውድቀት አቅጣጫ ሊያዝ ችሏል።

ለታሪካዊ ጉዞው መሰናክል የፈጠረበትን ሁኔታ ወደኋላ መለስ ብለን ስንመረምር በ1927 ዓ.ም ጠላት ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በነፃነቱ ፀንቶ የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ህልውና በከፍተኛ ፈተና ላይ በመውደቁ ነበር።

የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባለቤት እቴጌ መነን በወቅቱ የቤተክርስቲያኑ ገበዝ ነበሩ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ጠላትን አሸንፈው በድል እንዲመለሱ ከማይጨው ዘመቻ በፊት ለቅዱስ ራጉኤል ተሣሉ። ድሉ እንደተጠበቀው ሳይገኝ ሲቀር ለስደት በሚዘጋጁበት ጊዜ እንደገና ተሣሉ፤ ቅዱስ ራጉኤል በድል ከስደት ከመለስከን ቤተ መቅደስህን በዘመናዊ መልክ እሰራልሀለሁ ብለው የስዕለቱን ወረቀት ከአባ ሃና ጋር በመሆን ወደ እንጦጦ ራጉኤል ከመጡ በኋላ ፀሎት አድርሰው ደብዳቤው በፖስታ እንደታሸገ በታቦቱ ስር እንዲቀመጥላቸው አደረጉ። በድል ሲመለሱ ወረቀቱን ራሳቸው እንደሚወስዱትና ጉዳዩ በምስጢር እንዲጠበቅ በወቅቱ ለነበሩት ካህን አስጠነቀቁ በእርግጥም እንዳሉት በ1933 ዓ.ም በድል ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ደብዳቤውን ጠይቀው ወስደዋል።

ጣልያን ኢትዮጵያን ወርሮ በቆየበት ወቅት ራጉኤል ብዙ ተዓምራትን አሣይቷል፣ ቤተ መቅደሱን ሊደፍሩ የሞከሩትን የጣልያን ወታደሮችና አለቆቻቸውን ዝናምና ደመና በሌለበት ሁኔታ በተደጋጋሚ መብረቅ እያወረደ ፈጅቶአቸዋል። የጣልያን ባንዲራ በመብረቅ እየተመታ በመቃጠሉ እንጦጦ ላይ ማውለብለቡን እንዲተው አስገድዷቸዋል። በዚሁ መሠረት ጣልያኖች ጃንጥላ እየገዙ ለየአድባራቱ አበርክተዋል። ይህ ሁሉ ተዓምራት ከስለታቸው መስመር ጋር ስለተገጣጠመ እቴጌ መነን

www.ethiopianorthodox.org

የራጉኤልን ቤተክርስቲያን ህንጻ ለመሥራት ቆርጠው ተነሱ።

በዚህም መሠረት የመጀመሪያው እቅዳቸው ነባሩን የምኒሊክ ህንጻ አፍርሰው በምትኩ አዲስ ቤተክርስቲያን መሥራት ነበር። ሆኖም የምኒሊክ ቅርስ እንዳይፈርስ ተቃውሞ ስለተነሳባቸውና በምህንድስና ባለሙያዎች ጥናት የጥንቱን ቤተክርስቲያን ለማፍረስ ከባድ ወጪ እንደሚያስከትልባቸው ስለተነገራቸው አዲስ ቤተክርስቲያን በአዲስ አበባ ከተማ ለማሠራት ወሰኑ።

የቤተክርስቲያኑን ህንጻ ግንባታ ከማስጀመራቸው አስቀድሞ በእቴጌ መነን ሰብሳቢነት በእንጦጦ ራጉኤል ትልቅ ስብሰባ ተደረገ የስዕለቱ ደብዳቤ ለተሰብሳቢዎቹ ተነበበ። በስብሰባው ላይ እቴጌ ጣይቱ መነን ሃሣባቸውን ለውጠው ነባሩን ቤተ ክርስቲያን እንዲያድሱት በተሰብሳቢዎቹ ቢነገራቸውም ፈቃደኛ አልሆኑም። ስለዚህ ቤተክርስቲያኑ የሚሠራበትን ቦታ መምረጣቸውን ቀጠሉ፤ ቤተክርስቲያኑ አሁን የተሠራበትን ቦታ ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ወራሾች በስጦታ በማግኘታቸው በ1946 ዓ.ም በአቡነ ባስልዮስ ተባርኮ በንጉሠ ነገሥቱ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ።

በወቅቱ ፓትርያርክ የነበሩት አቡነ ባስልዮስ በተቃዋሚዎች ብጥብጥ እንዳይነካ በመንበረ ፓትሪያርክ ልዩ ስብሰባ አድርገው ካህናቱን ለማግባባት ሞከሩ። በተቃውሞ አቋማቸው የፀኑትን ከክህነት እንደሚያባርሩ አስጠነቀቁ። በዚህ ስብሰባ ላይ በከፍተኛ ስልጣን ላይ የነበሩ የደብሩ ታዋቂ ግለሰቦች ተሣታፊ ነበሩ። በታቦቱ መውረድ በተለይ የሱሉልታ አሮሞች ተቃውሞ ከፍተኛ ቢሆንም ተቃውሞውን በማርገብ ታቦቱ በ1948 ዓ.ም ወርዶ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ መነን በተገኙበት አዲሱ ቤተክርስቲያን ተመርቆ ታቦቱ እንዲገባ ተደረገ።

ከጽላቱም ጋር መላ ካህናቱ፣ አልባሳቱ፣ ዋና ዋና ቅርሶቹ ሁሉ ተሟጠው እንዲጓዙ በመደረጉ በአያሌ ኢትዮጵያዊያን መስዋዕትነት የተሠራው ቤተክርስቲያን እርቃኑን ቀረ። ይህ ነባር ታሪክ ሲፈርስ ተባባሪ የነበሩ አባቶች እንደነበሩ ሁሉ ተቃዋሚችም ነበሩ ይህም የአባቶች ተቃውሞ መሠረት ያለው በመሆኑ ለኃይለ ሥላሴ መንግሥት እስከ መጨረሻው አልበጀውም ።

በቤተክርስቲያኑ ላይ በደረሰው መናጋት ከ1948 - 60 ዓ.ም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር በመዘጋቱ የአካባቢው ነዋሪዎች ወልደው ክርስትና ለማስነሣት፣ የሞተ አስፈትተው ለመቅበር ወደ እንጦጦ ማርያም ለመሔድ የተገደዱበት ወቅት ነበር።

በ1960. ዓ.ም ባዕታ ለማርያም ገዳም የአፄ ምኒሊክ የሞት መታሰቢያቸው፣ እንጦጦ ራጉኤል የህያውነት መታሰቢያቸው እንደሆነ ታሪክን በመጥቀስ በተደረገው ስምምነት መሠረት የባዕታ ለማርያም ገዳም ፈለገ ብርሃን የተሰኘ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በእንጦጦ ራጉኤል ቅጥር ግቢ በማቋቋም መምህራኑና ተማሪዎች ከትምህርታቸው በተጓዳኝ ቤተክርስቲያኑን እንዲያገለግሉ በመደረጉ ለ12 ዓመታት ሲከፈትና ሲዘጋ የቆየው ቤተክርስቲያን መደበኛ አገልግሎት እንዲያገኝ ተደረገ። ይህም ውጤት ሊገኝ የቻለው ታሪክና ቅርስ በመጥፋቱና ይህም ታላቅ የአምልኮ ቦታ በመዘጋቱ ከፍተኛ ቁጭት ባደረባቸው እንደ አቶ መዝራዕተ አብ ሠርጤ በመሳሰሉ አባቶች ከፍተኛ ተጋድሎ ነበር።

ደብረ ኃይል እንጦጦ ራጉኤል ከዚያም ወዲህ ጥቂት ተቆርቋሪ ምዕመናን በሚያደርጉለት ድጋፍ ህልውናው ሊጠበቅ ቻለ እንጂ ከደረሰበት የታሪክ ስብራት ግን ሙሉ በሙሉ ሊያገግም አልቻለም። ቤተክርስቲያኑ በቤተ ክህነትም ዘንድ ትኩረት በማጣቱ ከ1948 - 1992 ዓ.ም ድረስ ለ44 ዓመታት አስተዳዳሪ እንኳን አልነበረውም።

ስለሆነም ለረጅም ዓመታት ተመልካችና አስታዋሽ አጥቶ በብቸኝነት በጫካ ውስጥ ተረስቶ በመቆየቱ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል። ቤተክርስቲያኑ በታሪኩና በበረከት ቦታነቱ ቀደምት ቢሆንም ከ44 ዓመታት በላይ በደረሰበት ሰው ሰራሽ በደል ለመታረዝና ለመጐሣቆል በውስጡ የሚገኙትም ትርፍራፊ ቅርሶች ለብልሽትና ለውድመት ሊዳረጉ በቅተዋል። ረጅም ዕድሜ ለአዲስ አበባ ምዕመናን እንጂ ህንጻውም ቢሆን ፈርሶ ወና ሆኖ በቀረ ነበር። ነገር ግን ቅዱስ ራጉኤል በሚያውቀው ምስጢር የሚሠሩለትን ምዕመናን ከሩቅም ከቅርብም እያስነሳ ቤተክርስቲያኑ እንዳይፈርስ በገንዘባቸው በጉልበታቸውና በዕውቀታቸው ያልተቆጠበ ተጋድሎ አድርገዋል። ከእነዚህም ታላላቅ የዚሁ ቤተ ክርስቲያን ባለውለታዎች መካከል አቶ ካሣኝ ምንልኬና በእርሳቸው አስተባባሪነት በቋርጠኝነት የተሠለፉትን የቀጨኔ ምዕመናን፣ አቶ ሳሙኤል ዐምደ መስቀል፣ አቶ አንዱአለም፣ ተክለ ህይወትንና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

የእንጦጦ ደብረ ኃይለ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን በቅርስነቱ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት ነው። ቤተክርስቲያኑ በአገር ቅርስነቱና በታሪክ ቦታነቱ ተመዝግቦ በበርካታ ቱሪስቶች ይጐበኛል። ይህም ለሀገሪቱ የወጭ ምንዛሪ በማፍራት ረገድ ያለውን ሚና ያመለክታል። በታሪክ ቦታነቱም የህንጻው አሠራር የኢትዮጵያ ሕዝብ ታታሪነት፣ ዐዋቂነትና ክሂሎት መግለጫ ሆኖ በግልጽ ይታያል። ስለሆነም ለቤት ክርስትያኑና ለቅርሶቹ መጠበቅ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በኃላፊነት መንፈስ መተባበር ትውልዳዊ ግዴታው ነው ።


www.ethiopianorthodox.org

# እንጦጦ /እንዶጥና/

ኢትዮጵያን ከዳር እስከዳር ለማስተባበርና በየጊዜው በጦርነት ምክንያት ቋሚ ቦታ በማጣት ከቦታ ወደቦታ የሚዘዋወረውን ሕዝብ አንድ ለማድረግ በመጣር አጼ ቴዎድሮስ ቀጥሎም አጼ ዮሐንስና አጼ ምኒልክ የመጀመሪያዎቹ ተጠቃሽ መሪዎች ነበሩ:: አገሪቱን አማክለው ለማስተዳደር ከክርስቶስ ልደት በፊትና በኋላ በኢትዮጵያ በርካታ በታሪክ የታወቁ ከተሞች የተመሠረቱ ሲሆን ከእነዚህም ታዋቂ ከተሞች መካከል እንጦጦ /እንዶጥና/ አንዷ ነበረች:: በዚህም መሠረት የእንጦጦ ታሪክ እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ እንደሚዘልቅ የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ::

በ1262 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበሩት አጼ ይኩኖ አምላክ ዋና ከተማቸው ቤተ አማሃራ /መካነ ሥላሴ/ አድርገው ሀገሪቱን ሲያስተዳድሩ በመሀል ሀገር የሚገኘው እንዶጥናህ ሁለተኛ ከተማቸው እንደነበር ገድለ ፊቅጦር ሰማዕቱ ላይ ተጠቅሷል::

ከዚያም አጼ ልብነ ድንገልና አጼ ዳዊት በ14ኛው ክፍለ ዘመን በአንዶጥናህ ላይ ከተማቸውን በማድረግ አገር ሲመሩ እንደነበር ስለግራኝ ወረራ በተጻፉት የታሪክ መጻህፍት ላይ ተመልክቷል::

አረብ ፋቂህ የተባለው የአረብ ታሪክ ፀሐፊ ስለግራኝ መሀመድ ወረራ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ኢትዮጵያዊው ንጉሥ አጼ ልብነድንግል በግራኝ ወረራ ወቅት ጦርነቱን መቋቋም ተሰኗቸው ከቦታ ወደቦታ በስደት ሲሸሹ እንዶጥናህ ላይ የተሠራው ትልቁ ቤተ መንግሥታቸው በእሣት ሲቃጠል ከርቀት አይተው አዘኑ በማለት የጻፈውን ማገሮር ኔራሲኒ በጣልያንኛ ቋንቋ ተርጉሞ ጽፎታል:: ይህንኑ መረጃ መሠረት በማድረግ ታዋቂው ኢ ትዮጵያዊው የታሪክ ፀሐፊ ተክለጻዲቅ መኩሪያ «የግራኝ አህመድ ወረራ» በተባለው መጽሐፋቸው እንዶጥናህ እየተባለ ሲጠራ የነበረው ከተማ የዛሬው እንጦጦ እንደሆነ እንዳንድ ጥናቶችን በማመሳከር ጽፈዋል::

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ከ500 ዓመታት በኋላ እንጦጦን በከተማነት እንዲመርጡና እንዲቆረቁሩ መነሻ የሆናቸውም ይኸው ታሪካዊ መሠረት ነው:: ንጉሡ ይህንን ታሪክ ለማወቅ ያስቻላቸውም አንድ መነኩሴ ዝዋይ ከዳሴቷ ገብቶ ከተመለከተ በኋላ የነበሩትን መጻህፍት ሁሉ ማውጣት ስላልቻለ ክብረ ነገሥት የተባለውን አንድ መጽሐፍ ይዞ እንደወጣ ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ «ታሪክ ዘዳግማዊ ምኒልክ» በተባለው መጽሐፋቸው ጠቅሰዋል:: መነኩሴው ይዞት የወጣው መጽሐፍ የአጼ ልብነ ድንግል ታሪክ የተጻፈበት ሲሆን ይህንንም ምኒልክ አይተው በሊቃውንት ሲያስተረጉሙ የቅዱስ ራጉኤልንና የእግዝእትነ ማርያምን አብያተ ክርስቲያናት በእንጦጦ ላይ ሠርተው እንጦጦን ዋና ከተማቸው ቢያደርጉ አገራቸውን በሰላም እንደሚያቀኑና ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ታላላቅ ታሪካዊ ድርጊቶችን እንደሚያከናውኑ ተገልጻላቸው:: በዚህ ም መሠረት የአባቶቻቸውን ከተማ አግኝተው በከተማነት መልሰው ለመቆርቆር ያደረጉት ድካም ቀላል እንዳልነበር ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ መስክረዋል:: ቦታው በትክክል እስከሚታወቅም ድረስ በወጨጫ ጋራ በፉሪ መካከል ከፍ ያለ ለከተማ የሚመች ሥፍራን አይተው ተቀመጡ:: በስተኋላም ደብረ ሊባኖስ ደርሰው ሲመለሱ ሱሉልታ ላይ ሆነው ጥንታዊዉ የእንጦጦ ከተማ ፍርስራሹ መገኘቱ ተነገሮአቸው በዚያው ወደሥፍራው በመሄድ ሲመለከቱ ዳዋ በቅሎበት አውሬ ሠልጥኖበት አገኙት:: ምልክቱንም ካገኙ በኋላ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በእኛ ጊዜ ከገለጠው ከተማዋን መልሰን እንሠራታለን በማለት የእንጦጦን ከተማ እንደቆረቆሩ ፀሐፊ ትዕዛዝ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው አስፍረዋል::

እንጦጦ በ1870 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ እንደተቆረቆረች እድገቷ ተፋጥኖ እስከ 50,000 ያህል ሕዝብ ሠፍሮባት እንደነበር ይነገራል:: በመጀመሪያ ከተማዋ ስትቆረቆር የድንኳን ከተማ የነበረች ስትሆን ኋላ ግን ለመሣፍንቱና ለመኳንንቱ ቋሚ የመሥፈሪያ ቦታ እየተደለደለ ጐጆ ቤቶች በየቦታው ተቀለሱ፣ በመሀልም የአጼ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ግራና ቀኝ የቅድስት ማርያምና የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያኖች ህንጻ ሥራ በቅደም ተከተል እንደተካሄደ ታሪኩ ያስረዳል::

እንጦጦን በከተማነት እንድትታጭ ያስቻላት ዋነኛው ምክንያት ከላይ የተጠቀሰው የታሪክ መሠረት ሲሆን ሌላው በመሀል ሀገር የምትገኝ አማካይና ከፍታዋም ለጦር ስትራቴጂ አመቺ ሆና በመገኘቷ ነበር:: አጼ ምኒልክ እንጦጦ ላይ ከሠፈሩ በኋለ ዙሪያውን ምሽግ አስቆፍረው ነበር:: ምሽጉ ማርያምና ራጉኤልን የሚያካትት ክብ ቅርጽ ያለው ነበር:: ግሊቸን የተባለ አንድ የወጭ አገር ሰው እንደጻፈው የምሽጉ ጥልቀት 12 ጫማ ሲሆን ስፋቱ ደግሞ 18 ጫማ ነበር ይላል፣ ወደ እንጦጦ ከተማ ለመግባትም ሁለት በሮች ብቻ እንደነበሩ ጽፏል::

የራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ከቤተ መንግሥቱ ጋር ተያይዞ በቅርበት እንዲሠራ ሲደረግ ዙሪያውን መሣፍንቱና መኳንንቱ እንዲኖሩበት ተደረገ:: አቡነ ማቴዎስና ራስ መኰንን ከቤተ መንግሥቱና ከራጉኤል ቤተ ክርስቲያን በስተደቡብ ምዕራብ፣ ዳጃች መሻሻ ወርቄ፣ አፈንጉሥ ነሲቡ ራስ ጉበና በስተሰሜን ምዕራብ፣ ራስ ሚካኤልና ራስ ተሰማ በስተደቡብ ምስራቅ፣ ጦረኛ ወልደየስ በስሜን ምስራቅ፣ ፀሐፊ ትዕዛዝ አለቃ ገብረ ሥላሴ ፊታወራሪ ሀብተ ገብርኤል፣ በስተምዕራብ፣ ዘበኛ



www.ethiopianorthodox.org

ሠፈር፣ ሥራ ቤት ሠፈር በምዕራብ፣ ካህናት በቤተ ክርስትያኑ ዙሪያ የቅዱስ ኤልያስ ቤተ ክርስትያን በምዕራብ፣ ሰሜን በር አካባቢ ባለው ኮረብታ ላይ ሲተከል ቱርክ ባሻ ታምሩ ከቤተ ክርስቲየኑ አጠገብ እንዲሠፍሩ ከተደረጉት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

እንጦጦ በዚህ መልክ ከተመሠረተች በኋላ ከተማዋ እንዳትሰፋና ወደፊት እንዳትራመድ ካገዷት ምክንያቶች መካከል አንዱ ውሃ በበቂ ሁኔታ አለመገኘቱ ሲሆን ለቤት ሥራ ደኑ በመመናመኑ ያስከተለው የማገዶ ችግር ነው። እነዚህም ችግሮች ከተማዋን ከእንጦጦ ወደ ዛሬዋ አዲስ አበባ እንዲዘዋወር ምክንያት በመሆኑ በ1878 ዓ.ም አዲስ አበባ በከተማነት ተቆርቁራ ነዋሪው እየለቀቀ በአዲስ አበባ ውስጥ መስፈር ጀመረ፣ የእንጦጦም ከተማነት እየቀዘቀዘ የዛሬውን መልክ ሊይዝ ችሏል።

እንጦጦ በእግዚአብሔር ኃይልና መሪነት የተገኘች ቦታ በመሆኗ በኢትዮጰያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ልዩ ቦታ አላት። ዳግማዊ ምኒልክ እንጦጦ ላይ በመጀመሪያ በመሥፈራቸው የኢትዮጵያ መዲና ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ ለመገኘት በቅታለች። እንጦጦ ማርያምና እንጦጦ ራጉኤል በዚህ ሥፍራ በመመስረታቸው ቦታው የቅርስና የታሪክ አምባ ለመሆን ችሏል። እንጦጦ በበቁ አባቶች ሱባኤና ጸሎት በብዙ ድካም የተገኘች ቦታ እንደመሆኗ ህሙማን ከውስጧ በሚፈልቀው ፀበል ከደዌያቸው የሚፈወሱባት ሥፍራ ለመሆንም ችላለች።

ለዓመታት በፈዋሽነታቸው የታወቁት የእንጦጦ ማርያም የእንጦጦ ራጉኤልና የሸንቁሮ ሚካኤል ፀበሎች ዛሬ ከምንጊዜውም በላይ ገነው በተለያዩ ደዌዎች የተያዙ ወገኖችን በመፈወስ ላይ መሆናቸው አንድ ምስክር ነው። እንጦጦ በእነዚህ ፀበሎች ምክንያት ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናትና ከውጭ አገሮችም ጭምር ከህመማቸው ለመዳን በሚመጡ ሰዎች በመጥለቅለቋ ዛሬ የሕዝቡ ብዛት ከአስር እጥፍ በላይ ጨምሯል። የቤት ግንባታዎች ተስፋፍተው ከተማዋ

የማደግ አዝማሚያ እያሣየች ነው።

እንጦጦ በታሪክ ሥፍራነቷ ብቻም ሳይሆን በሶሺዮ ኢኮኖሚ መስክም የራሷ አስተዋጽኦ አላት። እንጦጦ የጥበብ ምንጭ የሆኑ የአብዛኛዎቹ ሸማኔዎች መኖሪያ ናት። ለሸማ ሥራ ባለሙያዎች የሚያገለግል የተቀነባበረ የዲዛይን ዝግጅት እንደፈረንጆቹ አጠራር ካታሎግ ባይኖርም ሸማኔዎቹ ወይም የጥበብ ባለሙያዎቹ የሚያወጧቸው የጥበብ ዓይነቶች የተለያዩና እንደጊዜው ሁኔታ እየረቀቁና እያደጉ የሚሄዱ ናቸው። ይህም በመሆኑ እነዚህ የጥበብ ሥራዎች ተፈላጊነታቸው በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይወሰን በውጭ አገሮች ዜጎችም ዘንድ እየተወደደና ወደ ባህር ማዶም እየተጓዘ ነው።

በ1969 ዓ.ም የተጻፈ አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ እንደሚያመለክተው በወቅቱ አርባ አምስት ዓይነት የተለያዩ የጥበብ ዓይነቶች እንደነበሩ ተጠቅሷል። ከእነዚህም መካከል ልሙጥ ጥበብ፣ ድርብ ጥበብ፣ ቁርጥ ጥበብ፣ ዝም ጥበብ፣ ባለመቀስ፣ ባለደረጃ፣ ጨረር፣ የመስከረም አበባ ባለንብ አበበ ቢቂላ፣ የፈረስ ኮቴ፣ ቁልቢ፣ ሙሉኒሻን፣ ዓይነበጐ፣ ብርዋንጫ፣ ሦስት መደብ፣ ኢያሱ፣ ባለልብ ወዘተ ነበሩ። በወቅቱ የጥበቡ አሠራርና ተፈላጊነት የጐላ በመሆኑ አንድ ባለሙያ ከባለቤታቸው ጋር ኬንያ ናይሮቢ ላይ በተደረገው ታላቅ ኤግዚቢሽን ላይ አሠራሩን ለማሣየት ተሣታፊ ሆነዋል። ይኸው በአብዛኛው በእንጦጦ አካባቢ ባሉ ባለሙያ የጥበብ ሰዎች የሚሰራው የጥበብ ሥራ በተለያዩ አገሮች እየታየ አድናቆትን አትርፏል።

ከዚህም በላይ እንጦጦ የመስህብ ሥፍራ ናት፤ ከ 8000 ጫማ በላይ ከፍታ ያላት በመሆኑ ነፋሻማና በዙሪያው የሚገኘውን የመሬት አቀማመጥ ለመመልከትና ተፈጥሮን ለማድነቅ አመቺ ቦታ ነው። የአደስ አበባ ከተማን በስሜን፣ በምዕራብና በምስራቅ አጅቦት ለከተማው ደጀን ሆኖ ይታያል።

እንጦጦ የመዲናችንን የሌሊት ውብቷን ከጫፍ እስከጫፍ ለማየትና ለማድነቅ ምቹ የመመልከቻ ሥፍራ መሆኗን፣ በማየት በየዓመቱ የፈረንጆችን አዲስ ዓመት ተንተርሶ

www.ethiopianorthodox.org

የርችት ትዕይንት ለመመልከት በርካታ ቱሪስቶች ወደ እንጦጦ ይጐርፋሉ። ብዙ ጊዜ ቱሪስቶችና ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ ታላላቅ እንግዶች እንጦጦን ይጐበኛሉ። እንጦጦ በተለይ በጸደይ ወራት /መስከረም፣ ጥቅምት ህዳር/ ልዩ የተፈጥሮ ድምቀት ይታይባታል። በየጋራው፣ በየሸንተረሩ፣ በየሜዳው የሚያብበው አደይ አበባ ከመስኩና ከቡቃያው ልምላሜ ጋር ህብር ፈጥረው ከወፎች ዝማሬ ጋር በመዳመር ልብን ይሠርቃሉ።

መስከርም 1 ቀን በአዲስ ዓመት መባቻና መስከረም 21 ቀን በቅደም ተከተል የሚከበሩት የቅዱስ ራጉኤልና የእመቤታችን የእንጦጦ ማርያም በዓለ ንግሶች ተፈጥሮን በማድነቅና መንፈሣዊ ህይወት በመላበስ ድርብ ድርብርብ ደስታን ማትረፍ የሚቻልባቸው መልካም አጋጣሚዎች ናቸው። እንጦጦ በክረምት ወራት ቅዝቃዜውና ብርዱ ጥቂት ቢያስፈራም እንደብሉኮ የምትከናነበው ጉም ደግሞ ልዩ ውበት አለው። በዙሪያዋም እንደመቀነት የታጠቀችው የአጼ ምኒልክ በረከት የሆነው የባህር ዛፍ ደን ከተፈጥሮ ዕጽዋቶች ጋር ተዳምሮ ለአብዛኛው የአዲስ አሰባ ከተማ በማገዶነትና ለቤት ግንባታ ከሚያበረክተው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ሌላ ውበትና የነፋሻ ዓየር ምንጭ በመሆን የሚሰጠው ግልጋሎት ከፍተኛ ነው።

ይህ ሁሉ ውበትና ምቹ አቀማመጥ እምቅ ሀብት እያለ በእጅ ያለ ወርቅ እንዲሉ አንድም ኢንቬስተር አካባቢውን አለመቃኘቱ የሚያስገርም ነው። ባህር አቋርጠው የሚመጡ ቱሪስቶች ውሃ ጥማቸውን የሚቆርጡበት ንፁህ አየር እየተመገቡ ተመቻችተው የሚዝናኑበት ዓይን የሚገባና ደረጃውን የጠበቀ የማረፊያ ሥፍራ ባለመኖሩ ሊገኝ የሚችለው ጥቅም እየባከነ ነው፤ ስለዚህ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ በብርቱ ሊያስቡበት ይገባል እንላለን።

# እነማን ነበሩ ?

## ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ



ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ

ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ 1837 ዓ.ም በደብረ ብርሃን፣ ከአቶ ወልደ አረጋይና ከወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ተወለዱ:: በአንኮበር ከተማ ከሚገኙት መምህራን ዘንድ የቤተ ክህነት ትምህርት፣ ዜማና ቅኔ በሚገባ ተማሩ::

አለቃ ገብረ ሥላሴ በ1858 ዓ.ም ለወ/ሮ ባፈና ጸሐፊ ሆነው ሥራ ጀመሩ፤ ቀጥሎም በአለቃ ወልደ መድህን ስፍራ ተተክተው የንጉሥ ምኒልክ ጸሐፊ ትእዛዝ ሆኑ:: በተጨማሪም የርዕሰ አድባራት እንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው አስተዳደሪ ሆነው ተሾመዋል:: በዚም ሹመት የንቡረዕድ መዐረግ እስከ ተሾሙበት ጊዜ ድረስ ቆይተዋል:: በአስተዳደሪነት በነበሩበት ጊዜም፤ በነበረው የአስተዳደር ሥርዓት ከንጉሠ ነገሥቱ በማስፈቀድ ለሊቃውንቱ ርስት በማሰጠት የካህናቱን አስተዳደር መሠረት አሲዘዋል:: ለደብሩም ታላቅ ውለታ በመዋል ጥሩ ስም አትርፋዋል::

ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ በ1800 ዓ.ም በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚኒስትሮች ሹመት ሲሰጥ ሲቋቋም የጽሕፈት ሚኒስትር ሆነው

በዚሁ ዘመን በመጋቢት ወር፣ንቡረ እድ ዘደብረ ጽዮን ተብለው ተጨማሪ ሹመትና ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል:: ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በጽሕፈት ሚኒስቴር ሥልጣናቸው ለ40 ዓመታት ኢትዮጵያን እንዳገለገሉ የታሪክ ማህደር ያስረዳል::

ከብዙው ሥራቸው የማይዘነጋው በ1896 በግል ገንዘባቸው በንጉሥ ነገሥቱና በተለያዩ ሥዕላት በማስዋብ አጽፈው ያበረከቱት ድርሳነ ራጉኤል ምንጊዜም የማይረሳ ቅርስነቱን ይዞ ይገኛል:: በተጨማሪም «ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ» የተሰኘው የታሪክ ጽሑፋቸው በፈረንሣይኛ ቋንቋ ጭምር የታተመ በመሆኑ በዓለም ታዋቂ እንዳደረጋቸው ይነገራል::

ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ንጉሠ ነገሥታቸውንና ኢትዮጵያን ለረጅም ዘመናት ሲያገለግሉ ከኖሩ በኋላ ጥቅምት 27 ቀን 1905 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው በርእሰ አድባራት እንጦጦ ደብር ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ተቀበሩ፣ መካነ መቃብራቸው እስከ ዛሬ በመዘክርነቱ ይገኛል::

## ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት

ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ከድል በኋላ የመጀመሪያው የሸዋ ጠቅላይ ገገር ነበሩ፣ ቀጥሎም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ፣ የአገር ግዛት ሚኒስቴር፣ ምክትል ምኒስትር በመሆን ሠርተዋል:: ደጃዝማች ታከለ የእንጦጦ ራጉኤል ተወላጅና አገልጋይ ነበሩ:: የሚያውቋቸው የዓይን ምስክሮች ደጃዝማች ካባቸውን ደርበው ቅኔ ማህሌት ሲቆሙ እንደአሞራ ክንፍ አውጥተው የሚበሩ ይመስሉ ነበር::

❖ ❖ ❖

***አቶ ብርሃኑ ድንቄ***

አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ የታወቁት የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ሊቅ፣ የአለቃ ድንቄ ልጅ ናቸው:: ልጅየው አቶ



አቶ ብርሃኑ ድንቄ ከአሜሪካን ፕሬዝዳንት ኬኔዲ ጋር



www.ethiopianorthodox.org



ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት

ብርሃኑ ድንቄ የአባታቸውን ፈለግ በመከተል የቤተ ክህነት ትምህርትን በሚገባ አጠናቀው የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ቆይተዋል። አቶ ብርሃኑ ድንቄ በዘመናዊውም ትምህርት እንግሊዝኛ፣ፈረንሣይኛና ጣሊያንኛ ቋንቋዎች አሣምረው ይችሉ ነበር። በአስተዳደር ችሎታቸው ተመርጠው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በጽህፈት ምኒስቴር ዋና ዳይሬክተር በፖስታ፣ቴሌግራፍ፣ ቴሌፎን ሚኒስቴር ም/ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ከተማ ም/ከንቲባና ከዚያም በአሜሪካ የኢትዮጵያ ን/ነ/መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን አምባሳደር በመሆን ሠርተዋል። አቶ ብርሃኑ ድንቄ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ከሆኑም በኋላ ከእንጦጦ ራጉኤል ካህናት ጋር በመሆን ከመንፈሳዊ አገልግሎት የራቁበት ጊዜ አልነበረም። በተለይም በተቀጸል ጽጌ በዓል ላይ በተደጋጋሚ በመገኘት ንቁና ተደናቂ ተሣታፊ ነበሩ።

⁜ ⁜ ⁜

*አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ*

አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ፣ አቶ አካለወርቅ ሀብተ ወልድ፣ ፀሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ፣ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የራጉኤል የመጀመሪያው ትክለኛ የነበሩት የደብተራ ሀብተ ወልድ ልጆች ናቸው።

አቶ መኰንን ሀብተወልድ በድኅ፣በጸመ ድኅ፣ የታወቁ ሊቅ ነበሩ። አቶ መኰንን ዘመናዊ ትምህርት በመቅሰም ወደ መንግሥት ተቋም ሥራ ከተዘዋወሩ በኋላ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር



ከግራ ወደቀኝ አቶ መኮንን ሀ/ወልድ ፣አቶ አክሊሉ ሀ/ወልድ አቶ አካለ ወርቅ ሀ/ወልድ

የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የአገር ግዛት ምኒስቴር በመሆን በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሠርተዋል። ሀገራቸውን እጅግ በጣም ይወዱ ስለነበር በወጣቱ ትውልድ ውስጥ የሀገር ወዳድነትን መንፈስ ለማስረጽ የሀገር ፍቅር ማህበርን አቋቁመዋል። እንዲሁም «ጥጥ ትክሉ ሸማ ፍተሉ» እያሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሙያ እንዲማር ይሰብኩ ነበር። ኢትዮጵያውያን በንግድ ሥራ ተሠማርተው በባእዳን እጅ የነበረውን የንግድ ሥራ እንዲቆጣጠሩ በማበረታታት ውጤት ያስገኙ ከእንጦጦ ደብረ ኃይል ዕንቁዎች አንዱ ነበሩ።

*ፀሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ*

ፀሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ሌላው የእንጦጦ ራጉኤል ተወላጅ የነበሩ ሀገራቸውን በመጀመሪያ በውጭ ጉዳይ ምኒስትርነት በማገልገል በዲፕሎማሲውመስክ የኢትዮጵያን ጥቅም በማስጠበቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ ችሎታቸውንና ብልህነታቸውን ያስመሰከሩ ታዋቂ ዲፕሎማት ነበሩ።

ፀሐፊ ትእዛዝ አክሊለ ሀብተ ወልድ በሥራ ብቃታቸውና ችሎታቸው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጠቅላይ ምኒስትር በመሆን ሠርተዋል።

እንጦጦ ራጉኤል ኮትኩቶ ለቁም ነገር ያበቃቸው ምሁራን እነዚህ ብቻ አልነበሩም። አፈንጉሥ ገብረ ክርስቶስ የታወቁ የፍትሀ ነገሥት ተርጓሚ፣ብላታ ኪዳኔ መልክ ጸዴቅ አፈንጉሥ፣ ፊታውራሪ ሣህሉ ወልደ መድህን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ አለቃ ዓይናለም ገብረማርያም ደራሲና ጋዜጠኛ ይገኙባቸዋል። የእነዚህን ታላላቅ የሀገር ምሁራንና መሪዎችን ታሪክ ወደፊት በተከታታይ በስፋት አቅርበን የምናስነብባችሁ ይሆናል።


www.ethiopianorthodox.org

# -ጎሩይ-

## ከእንጦጦ ደብረ ኃይል ራጉኤል ጣፋጭ ፍሬዎች አንዱ

*እጅጉ ረታ*

የዛሬን አያድርገውና፣ እንጦጦ ራጉኤል የንጉሠ ነገሥቱ መዲና በነበረበት ጊዜ ፣አዬ ! ደብረ ኃይል ራጉኤልን ያየ:: እንዲህ እንደ አሁኑ ጭር ያለ ደብር ሳይሆን ፣ በተለያየ ሙያ የተካኑ ታላላቅ መምህራን የተሰባሰቡበት፣ መንፈሳዊው ትምህርት ከንባብ ቤት እስከ ትርጓሜ መጻሕፍት ደረጃ በደረጃ የሚሰጥበት፣ ብዙ ደቀ መዛሙርት የወጡበት ታላቀ ደብር ነበር::

ደብረ ኃይል እንጦጦ ራጉኤል በትምህርት ወልዶ፣ በጥሩ ሥነ ምግባር ኮትኩቶ ያሳደጋቸው ደቀ መዛሙርት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ብቻ አልነበሩም:: በዕውቀታቸው ፣ በችሎታቸው ታጭተው፣ ተመርጠው በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ ተመድበው, ሀገራቸውንና ወገናቸውን በቅንነት፣ በታማኝነት ያገለገሉ ታላላቅ ሰዎችም አፍርቶአል::

ከነዚህም አንዱ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ናቸው:: ታላቅ ምሁር፣ ዲፕሎማት " የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ አባት "የተባሉት ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ እዚህ ደረጃ የደረሱት እንዲህ በቀላሉ አይደለም ፤ ብዙ የሕይወት ውጣ - ውረድ አልፈው ነው:: ይህንኑም በዚች አነስተኛ ጽሑፍ ላይ ባጭር በአጭሩ ብቻ ለማሳየት እሞክራለሁ::

ኅሩይ የሚለው ስም የወጣላቸው ግን ከቀን በኋላ ስለሆነ፣ ታሪካቸውን የምጀምረው ቀድሞ ከወጣላቸው ገብረ መስቀል ከሚለው ስማቸው በመነሣት ይሆናል::

ገብረ መስቀል በመርሐ ቤቴ ውስጥ፣ ደን አቦ በተባለ ሰበካ በ1871 ዓ.ም. ተወለደ:: በ40 ቀኑ ሥርዓተ ጥምቀት ሲፈጸምለት ገብረ መስቀል ተባለ ፤ በ7 ዓመቱ እዚያው እቀዬው ፣ ከየኔታ ሥነ ጊዮርጊስ ዘንድ ፣ ፊደል ቆጥሮ በ9 ዓመቱ ዳዊት ደግመ ፤ ውዳሴ ማርያም፣ መልክዓ ማርያም፣ መልክዓ ኢየሱስ በቃሉ አጠና::

እናቱ ወ/ሮ አመተ ማርያም ይባላሉ ፤ መንዜ ናቸው - ነገሥታቱ ባንድ በኩል የሚወለዱበት ጠል የማደሬ ወገን :: አባቱ ግን መርሐ ቤቴ አገሪት በተባለ ቦታ ይወለዱ እንጂ ፣ የትውልድ አገራቸው ሳይንት ነው-ወደያ ሩቅ:: አልተማሩም፣ ጨዋ ባላገር ናቸው:: ገብረ መስቀልን የወለዱት 40 ዓመት ቆይተው ሚስት ካገቡ በኋላ በመሆኑ እንደ ብርቅ ልጅ ያዩታል::

ለክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ዕድል መቃናት ዋናው ምክንያት አባታቸው አቶ ወልደ ሥላሴ በመሆናቸው፣ ይህንኑ እዚህ ላይ ሳልገልጸው ማለፍ አልፈልግም::

የደን አቦ ደብር ዕልቅናው የወይዘሮ ባፌና ነው፣ ቀድሞ የንጉሥ ሚኒልክ ሚስት- ከእቴጌ ጣይቱ በፊት :: አቶ ወልደ ሥላሴ ምንም ትምህርት ባይኖራቸው በተፈጥሮ ብልኅ፣ ዐዋቂ ፣አርቆ አስተዋይና ጠንካራ ሰው መሆናቸውን ወይዘሮይቱ ስለሚያውቁ፣ ስንቱ የተማረ ካህን እያለ የሾሙ አቶ ወልደ ሥላሴን ነው::



አቶ ወልደ ሥላሴ የዋዜማውን ይሁን የዋናውን በዓል ድግሥ በሚያበሉ በሚያጠጡበት ጊዜ፣ ወደ ኋላ ዘግይተው ከመጡት ካህናት አንዱ የሆኑትን ደብተራ አውላቸውን አሳላፊዎች ያስቀመጡዋቸው እተገኘው ቦታ ነው:: ደብቴ እንዴት ብናቅ ነው ብለው ነደዋል ፤ ጦፈዋል::

ታዲያ አቶ ወልደ ሥላሴ እየተዟዟሩ "በሉ እንጂ አባቶቼ ተጋበዙ " እያሉ አጠገባቸው ሲደርሱ፣ ደብተራው ቱግ ይሉና የስድብ መዓቱን ያወርዱባቸዋል::

አቶ ወልደ ሥላሴ ግን መልስ አልሰጡአዋቸውም ፤ ብስጭትና ንዴታቸውን በሆዳቸው ይዘው ወደ ውጭ ይወጣሉ:: ከሁሉም ከሁሉም አቶ ወልደ ሥላሴን ክፉኛ ያቈሰላቸው፣ " ዳሩ አንተ ምን ታደርግ ? ነገሩ የተበላሸው ፣ ወ/ሮ ባፌና አንተን ደንቆሮውን መሀይም ኀላፊ አድርገው የሾሙ ዕለት ነው "የሚለው ነገራቸው ነበር::

ከዚያ እንደወጡ ወደ ጓሮ ዞረው ከጉተራው ሥር ትክዝ በማለት ይቀመጡና መሬቱን በእግራቸው ሲቆረቍሩ ወ/ሮ አመተ ማርያም ያገኙአቸዋል:: ምን ነገር እንደገጠማቸው ሲጠይቁአቸውም፣ ደብተራ አውላቸው የሰደቡአቸውን ይነግሩአቸዋል:: ሚስትም ቀበል ያደርጉና፣ "ታዲያ ለዚህ ምን ያበሳጫል ፤ ዛሬማ ልጃችን ደርሶ ዳዊት ደግሞ የለ ? ይበሉ ይነሡና እቤት እንግባ› በማለት ነገሩን " ያቃልሉታል:: እውነትም ለካ ቁጭታቸውን የሚወጡበት ልጅ እቤት አለና::

አቶ ወልደ ሥላሴ በልጅነታቸው ሳይማሩ በመቅረታቸው ቀድሞውኑ ቁጭቱ በሆዳቸው ስላለ ፣" አምላኬ ልጅ የሰጠኝ እንደሆነ፣ ለትምህርት ወደ ከተማ እሰደዋለሁ እንጂ ፣ በባላገር አላኖረውም " የሚል ምኞት ነበራቸው:: ገብረ መስቀልን እስካሁን እቤት ያቆዩት ትንሽ ከፍ ይበል፣ ሰውነቱም ይጥና፣ ብለው እንጂ ፣ ወትሮም ቢሆን እንዲህ ባጭሩ እንዲቀር የሚያስቡ ሰው አልነበሩም::

ስለዚህም ጊዜ ማጥፋት አልፈለጉም:: የሚቀጥለውን ትምህርት ወደሚያገኝበት ቦታ ይዘውት ለመሄድ አሰቡ፤ ወዲያው ደግሞ አንድ ነገር መጥቶ ከፊታቸው ድቅን አለ:: ወዲህ እንደ ዐይናቸው ብሌን የሚሳሱለት ወዲህም ተምሮ ነገ ትልቅ ሰው ይሆንልኛል ብለው የሚጓጉለት አንድ ፍሬ ልጅ ሆድ ይብሰውና ከትምህርቱ ቢዘናጋስ ብለው ፈሩ ፤ ጭርሱን ቢተወውስ ብለውም ሠጉ:: ወዲህም ይራብ ይጠማና ፣ ይታረዝ ይቸገርና፣ይጎዳብኛል ብለው ክፉኛ ተጨነቁ:: ስለዚህ የቀረ ይቀራል እንጂ ልጄን ብቻውን እልከውም በማለት አብረውት ለመ ሄድ ቈረጡ::

ከዚያም በጉተራ ካለው እህል የሚሸጠውን ሸጠው ለቤተ ሰቡ



www.ethiopianorthodox.org

የሚቀረውን አስቀርተው ስንቃቸውን ቋጥረው ፣ ትዳራቸውን፣ ቤት ንብረታቸውን እርግፍ አድርገው ትተው፣ ባለቤታቸውንና ታናናሽ እህቶቹን፣ ሁለቱን ሴት ልጆቻቸውን ተሰናብተው በጠፍ ጨረቃ ደን አቦን ለቀቁ:: ከዚያም ወደ ሰላሌ አቀኑ:: ገብረ መስቀልንም ወስደው ከስሬ መድኃኔዓለም ገዳም ትምህርት ቤት አስገቡት::

የ10 ዓመቱ ልጅ ገብረ መስቀልም እንደ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠረውን የዜማ ትምህርቱን ቀጠለ:: አቶ ወልደ ሥላሴም እዚያው ስሬ መድኃኔ ዓለም ተቀመጡ::

በዚያን ዘመን- ምን በዚያን ዘመን ብቻ - ከዚያን በፊትም ሆነ በኋላ ፣ ያገር ቤቱን ትምህርት መማር የሚፈልግ ተማሪ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ ለመቀጠል ሲፈልግ ከአባት ከእናቱ ኰብልሎ ይሄዳል እንጂ ፣ ርቆ ሄዶ እንዲማር የብዙዎቹ ወላጆች ፍላጎት አይደለም:: ጥቅሙ የገባው አንዳንድ ወላጅ ቢኖር እንኳን፣ ስንቁን አስይዞ ይሰደዋል ወይም በጣም የሚወደው ልጁ ከሆነም አድርሶት ይመለሳል ፤ አልፎ አልፎም እየሄደ ይጠይቀዋል እንጂ፣ ልጀ ይራብ ይጠማብኛል ፤ ይታረዝ ይቸገርብኛል ብሎ የሞቀ ቤት ንብረቱን ትቶ ለልጁ ትምህርት ሲል ፣ ከሀገር ወጥቶ ከልጁ ጋር አብሮ የተቀመጠ ሰው ፣ ከነሀ አርቆ አተዋይ ደግ አባት በቀር ሌላ ሰው መኖሩ ከዚህ በፊት አልተሰማም ፤ የእርሳቸው የተለየ ነው::

አብዛኛው ባላገር ከልጁ የወደፊት ጥቅም ይልቅ የራሱን በማስቀደም፣ ባለ ከብቱ ከብቱን እንዲጠብቅለት ሌላ ሌላውም አጠገቡ ሆኖ የኑሮ ትግሉን እንዲካፈልለት ይፈልጋል እንጂ፣ ከአጠቡ ርቆ እንዲማር አይፈልግም::

ሌላው ደግሞ ልጀ የቄስ ትምህርት የተማረ እንደሆነ፣ ፈሪ ይሆንብኛል በማለት ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ መማሩን አይፈቅድም:: ፈሪነቱን ለማሳየትም:-

የተማሪ ወዳጅ ቢቀር ምናባቱ፣
ጕራዴው ሲመዘዝ ይላል በአዛኙቱ፤
እየተባለ ይዘፈንበታልና::

አንዳንዱ ደግሞ እኔ አባቱ ቤት እንጀራው ሞልቶ ተርፎ፣ ልጀ በሰው ሀገር ሄዶ ለምኖ ሊበላ ? ለቁራሽ እንጀራ ብሎ ከውሻ ጋር ሲታገል ሊኖር ? ሲሆን ሲሆን የንጉሥ፣ ሲታጣ ሲቀር የራስ የደጃዝማች አሽከር ሆኖ ይኖራል እንጂ፣ ምን በወጣው ተማሪ ይሆናል እያለ የሚኰራራም አለ::

በእንተ ስማ ለማርያም ሲባል ከሀብታም ውሻ ጋር ያለውም ትግል አያድርስ ነው- መፈጠርን ያስጠላል:: በዚህ የተመረረ ፣ የተከፋ ተማሪ :-

እናቴ ባየሽ ፣ እህቴ ባየሽ ፣
ለቁራሽ እንጀራ ሲያባርረኝ ውሻ ፤- አለ ይባላል::

እንግዲህ አቶ ወልደሥላሴ ይኼን ፣ ይኼን ችግር ቀደም አድርገው ስለሚያውቁት ልጃቸውን እንዲህ ያለው ነገር እንዲጠብቀው አልፈጉም፤ ስለዚህም ለልጃቸው ትምህርት ሲሉ ብቻ ፣ በሰው ሀገር መከራ መቀበልን መረጡ:: አሁን ይህን ማ አድርጐት ያውቃል? ትልቅ መስዋትነት ነው::

አቶ ወልደሥላሴ እንዲህ ያለውን መስዋትነት ባይከፍሉ ኖሮ፣ አሁን ማይሙት፣ ትንሹ ልጅ ገብረ መስቀል በዚያ ለጋ ዕድሜው፣ ከእናት-ከአባቱ ቤት ኰብለሎ ወጥቶ ያን ሁሉ ችግርና መከራ አልፎ ፣እንደተመኙለት ትልቅ ሰው፣ የንጉሥ ባለሟል ፣ ብላቴን ጌታ ፣ሚኒስትር፣ አንቱ የተባለ ደራሲ ይሆን ነበር ? ጎሩይ የሚለውስ ስም በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ሰማይ ላይ የአጥቢያ ኮከብ ሆኖ ያበራ ነበር ? እንጃ አይመስለኝም ::

ቀለም የማይመልሰው ገብረ መስቀል የዜማ ትምህርቱን ያጣድፈው ጀመር:: ዓይነ ስውር መምህሩ የኔታ በሻህ ተከሥተ እስኪደነቁ ድረስ ፣ሰላም ለኪ ብሎ የውዳሴ ማርያምን ዜማ በሁለት ወር ብቻ አቀላጠፋት:: ከዚያም አርባዕት፣ አርያም መስተጋብእ የተባለውን ለአንድ ዓመት ያህል በዜማ ጮኸ (ተማረ):: ሁሉም የቃል ትምህርት ነው:: ከየኔታ ገብረ ሥላሴም የቤተ ልሔሙን (የያሬድ) ጾመ ድጓ ዜማ እዚሁ በአጭር ጊዜ ፈፀመ ::

ብልኅና ከማንም ሰው ጋር በቀላሉ ተግባቢ የሆነው ገብረ መስቀል የእጅ ጽሕፈት ሙያ ለመማር ከፍ ያለ ጉጉት ነበረው:: እዚያው ት/ቤት በትርፍ ጊዜው በገዛ ጥረቱ ጽሕፈት የተማረ ኃይሌ የሚባል ልጅ ስለ ነበር ፣ እርሱን ተጠግቶ ከጭላትና ከዕፀ ፋርስ ቀለም አዘጋጅቶ የበሬ ብራኳ አሰናድቶ የእጅ ጽሕፈት ለመማር ጊዜ አልወሰደበትም :: አቶ ወልደ ሥላሴ ቀለም ተቀባይነቱን ብቻ ሳይሆን፣ ጽሕፈት ማወቁን በማየታቸው የሚሰማቸውን ደስታ መገመት አያዳግትም::

የስሬ መድኃኔ ዓለም ባለጕልት ወ/ሮ ፀሐየ ወርቅ ዳርጌ፣ የገብረ መስቀልን ብልኅነት የአባቱንም መንፈሰ ጠንካራነት በማየታቸው ለለት ጉርስና ላመት የሚሆን ቀለብና ደመወዝ እንዲሰጣቸው ስለፈቀዱ በዚህ በኩል ያለው ችግር ተቃለለ ፤ እንደ ተፈራው አልሆነም::

አባትና ልጅ በዚህ ሁናቴ ሁለት ዓመት ያህል እንደቆዩ፣ አቶ ወልደ ሥላሴ ፣ የዓለሙን ነገር ቀደም አድርገው ትተውታልና፣ በ53 ዓመታቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደው ከመ ነኩሱ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ልጃቸው ተመለሱ::

ልበ በሽተኛ ስለ ነበሩም በየጊዜው ለጠበል ወደ ደብረ ሊባኖስ ይመላለሱ ነበር ፤ በሽታው ሥር እየሰደደ በሙሄዱም፣ ለጸበል እንደሄዱ እዚያው ዐረፉና መርዶው ለገብረ መስቀል መጣለት::

ገብረ መስቀል ዕንባውን በአባቱ መቃብር ላይ ለማፍሰስና እርሙን ለማውጣት በሄደ ጊዜ፣ የአባ ወልደ ሥላሴን ኑዛዜ የተቀበሉት የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ አባ ወልደ አቢብ የነገሩት ሌላ ነገር ሳይሆን፣ " ልጀ ትምህርትህን ሳትጨርስ ወደ ሀገርህ እንዳትመለስ ዐደራ ፣ዐደራ" የሚል ነበር:: ገብረ መስቀልም ይህን ዐደራ እስከ ዕለተ ሞቱ ጠብቆታል፤ የሙት ቃል ተፈጻሚ ነውና- ክቡር::

ገብረ መስቀል ከደብረ ሊባኖስ ተመልሶ ትምህርቱን በሚከታተልበት ጊዜ፣ የከብት ዕልቂት በሽታ በሀገሩ ስለገባ፣ ከወይዘሮ ፀሐየ ወርቅ የሚሰጠው ቀለብ ተቋረጠ::ይህ ደሞ ለ13 ዓመቱ ልጅ ትልቅ ፈተና ሆነ :: ሌላ አማራጭ የለውም ፤ ትምህርቱን ማቋረጥ ግድ ሆነበት:: ያቺን ክፉ ቀን ለማሳለፍም ሲል ወደ ያያ ጉለሌ ሄደ::

እዚያም የሰሞን መሬት ትክለኛ የሆነ አንድ ሰው ሆዱን ብቻ ችሎ በዲቁና ለማገልገል ተዋዋለው:: ቀኒቱ ክፉ ቀን አይደለች? ገብረ መስቀል ለባለጉዳዮች እየጻፈም፣ ተቍርሳ በተሰጠችው ትንሽ መሬት ላይ እያረሰም ኑሮው መሻሻል ሲጀምር፣ ፊታውራሪ በላይነህ የተባሉ ሰው አባ ብለው ወደ ሊሙ ወሰዱት::

እዚያም ብዙ አልቆየም፤ ሊሙ አጠገብ እንደቆር ወደ ተባለ ቦታ ሄዶ ቀኛዝማች መቁረጭ ለተባሉ ሰው የጌታ አደረ (አሽከር ሆነ) ::

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ቀኛዝማች አዲሱ አሽከራቸው ገብረ መስቀል ጽሕፈት ማወቁን ይሰማሉ:: ከአስጠሩት በኋላም ደብዳቤ ለሰው እንዲጽፍላቸው ይጠይቁታል:: በዚያ የልጅ ዕድሜው ፣ እንዲያ አሳምሮ የጻፈውን ባዩ ጊዜ፣ እጅግ ተደነቁ:: "ስምህ ከዛሬ ጀምሮ የሆነው ፍሬ ነው ፤ ገብረ መስቀል አይደለም " ብለው አዲስ ስም አወጡለት::

ከዚያን ጊዜ አንሥቶም ራት ምሳው ከቀኛዝማች ጋር ከእልፍኝ ሆነ፤ አከበሩት ፤ ከፍ ከፍ አደረጉት- በሙያው:: መግባባቱ፣ ይበልጥ መቀራረቡና መዋደዱም ሥር ሰደደ:: ይልቁንም ይህ ልጅ ፣ በዕለተ ሰንበትና በበዓላት ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄደ በዲቁና ያገለግል ነበርና ቀኛዝማች በዚህም ይበልጥ አደነቁት ፤ ወደዱት ::

የንስሐ አባታቸው ግን የዚህን ልጅ ነገር አልወደዱለትም:: ታዲያ አንድ ቀን ፣ "ልጅ እኮ ከአዋቂ ጋር አብሮ መሶብ መቅረብ የለበትም ፤ ምንም ቢወዱት መመገብ ያለበት ለብቻው ነው" ይሉአቸዋል::

ቀኛዝማች ቄሱን ክፉኛ ታዝበዋቸው፣ "ምነው እርስዎ በቅስና ፣ እሱ በዲቁና በአንድ መቅደስ ትቀድሱ የለ ?" ብለው ሲጠይቋቸው ፣ "አዎን" ይሉአቸዋል:: "ይህ ከሆነ ታዲያ ከጌታ ማእድና ከእኔ ማእድ የማን ይበልጣል ?" ሲሉ እንደ ገና ይጠ


www.ethiopianorthodox.org

ይቋቸዋል:: "እሱማ የጌታ ይበልጣል " ይላሉ ቄሱ:: "እንግዲህ ይህን ካመኑና የሆነው ፍሬ ካለበት ማእድ አልቀርብም ካሉ ለብቻዎ ይሠራልዎታል እንጂ ፣እሱማ ከእኔ አይለይም " ቁርጥ ያለ አጭር መልስ:: እንዲያው እንዴት ያሉ አስተዋይ ኖረዋል?

በዚህ ጊዜም የዐድዋ ጦርነት ዘመቻ ታወጀ:: ቀኛዝማችም የሆነው ፍሬን ለባለቤታቸው አደራ ብለው ለዘመቻው ሲነሡ፣ የሆነው ፍሬ እስከ አዋሽ ሸኝቶ፣ በቸር ይመልስዎ በማለት ጉልበት ስሞ ተመለሰ::

የሆነው ፍሬ የቅዳሴ ቤቱን በዓል ለማክበር ወደ በርጋ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል:: እዚያም ከእንጦጦ ራጉኤል ደብር በመጡት አራት ካህናት ዜማ እጅግ ይመሰጥና ትምህርቱን በማቋረጡ ክፉኛ ተቆጨ ::

ከክብረ በዓሉ መልስ፣ የሆነው ፍሬ ፈራ - ተባ እያለ ፣ ወደ አንደኛው ጠጋ ብሎ፣ አብሮአቸው ሄዶ ትምህርቱን እንዲቀጥል ይፈቅዱለት ዘንድ በተለመደ ትሕትናው ጠየቃቸው::

እነርሱም ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ፣ " ይሁን መሄዱንስ ሂድ፤ ግና የአዲስ አበባን ብርድና ረሀቡን ትችለዋለህ ?" አሉት:: ረጋ ብሎ "ፈጥሮኝ የለ?" ነበር መልሱ-አጭር :: "ልጄ አንተ በለጥከኝ " አሉት በመልሱ የተገረሙት መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ::

በጉዞ ላይ ሳሉ ፣ "የሆነው ፍሬ" የተባለበትን ምክንያት መምህር ሲጠይቁት፣ የድሮ ስሙ ገብረ መስቀል እንደ ነበረና ይኸኛውን ስም ያወጡለት ግን፣ ቀኛዝማች መቁረጭ መሆናቸውን ተናገረ:: በዚህ ጊዜ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ቀበል ያደርጉና "እኔ ለትምህርት ወደ ጎንደር ስሄድ ስሜ ኀሩይ ነበር፤ አንተም እንግዲህ በል በዚሁ ስም ተጠራበት" አሉት - በሰጣቸው መልስ ተገርመዋልና:: ኀሩይ ማለትም ምርጥ፣ የተመረጠ ማለት ነው:: በዚህ ስም ዳዊትም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ተጠርተውበታል - በጌታ:: ይህ ስም ከዚህ በኋላ አልተወጠም ፤ በክብር ላይ ክብርን ፣ በማዕረግ ላይ ማዕረግን እየጨመረ ፣ ከኢትዮጵያም አልፎ በሠለጠነው ዓለም ሁሉ መጠሪያ ስማቸው ሆነ::

ኀሩይ እንጦጦ ራጉኤል ከደረሱ በኋላ፣ ታህሣሥ 1 ቀን 1888 ዓ.ም. ልክ በ16 ዓመት ከ7 ወር ዕድሜ ያቸው «አእመረ» ብለው ጀምረው ፣ ሌሎቹን ቀድመው በ9ነኛ ወራቸው "ይበል! ይበል!" ያሰኘ ቅኔ ተቀኙ- ተደነቀላቸው:: የቅኔ መምህራቸው የኔታ ሰውዬ ይባላሉ ፤ የጎጃም አገር ሰው ናቸው::

አንድ ደቀ መዝሙር ጥልቅ ምስጢር ያለበትን፣ ከባድ ምርምርና ጥናት የሚጠይቀውን የቅኔ ትምህርት ከነአገባቡ ፈጽሞ ተመረቀ ማለት፣ የማስትሬት ዲግሪውን ተቀበለ ማለት ነው::

ኀሩይ በዚህ አላበቁም:: ከዚህ የሚቀጥለወን የመጻሕፍት ትርጓሜ ተያያይዙት:: በዚህ ጊዜ መምህራቸው ፣ኀሩይ የሚለውን ስም የሰጡአቸው ፣ የመጻሕፍተ ሐዲሳት ባለቤት (ሊቅ) የሆኑት የኔታ ወልደ ጊዮርጊስ ነበሩ:: ኀሩይ በቀለም ተቀባይነታቸው ብቻ ሳይሆን፣ በጠባያቸውም ትሑትና ተግባቢ ስለ ሆኑ መምህራቸው እጅግ ወደዱአቸው:: በሁለቱም መካከል ያለው ፍቅር በወላጅ አባትና ከአብራክ በተከፈለ ልጅ መካከል እንዳለው ያለ ፍቅር ነበር:: አቶ ወልደ ሥላሴን የወሰደባቸው አምላክ፣ መምህር ወልደ ጊዮርጊስን ሌላ አባት አድርጎ ሰጣቸው ማለት ነው:: ከሌሎች አብልጠው ይወዱአቸዋል፤ ከዚህም የተነሣ ማደሪያቸውም፣ ምግባቸውም ከመምህራቸው ጋር ሆነ:: "ፈጥሮአቸው የለ?" - አልጣለቸውም::

የውዳሴ ማርያምን ትርጓሜ (በአንድምታው ማለት ነው)በ3 ወር ብቻ አጠናቀቁ - በቃል:: አፍጥ ነውታል:: ከዚያም መጻሕፍተ ሐዲሳትን (ሀያ ሰባቱን ሁሉ) በአንድምታ ትርጓሜ ፣በ4 ዓመት ብቻ ዳር እስከ ዳር አጠኑት :: ይኼም ፈጥኖአል::

በአጠቃላይ የትርጓሜ መጻሕፍት (ብሉይ፣ ሐዲስ፣መጻሕፍተ ሊቃውንት፣ መጻሕፍተ መነኮሳት) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የሚጠኑት፣ ዘራቸው (ንባባቸው) ብቻ ሣይሆን ትርጓሜአቸውም፣ ሐተታቸውም ወዘተ ጭምር ሆኖ ፣ሁሉም የሚጠናው በቃል ነው:: እንዲህ እንደ ዘመናዊው ትምህርት መጽሐፍ እያገላበጡ ማስታወሻ እየያዙ አይደለም - ነውር ነው:: እያንዳንዳቸውን አጥንቶ ለመጨረስም፣ ቢያንስ ቢያንስ አምስት ስድስት ዓመት ይፈጃል - በትንሹ :: ኀሩይ ይህን እንደ ፈጸሙ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ከዳግማዊ ምኒልክ ዘንድ ቀርበው ባለወርቀ ዘቦ ቀሚስ ተሸልመዋል::

በዚህ ብቻ አላበቁም:: ደግሞም እዚያው ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ዘንድ መጻሕፍተ ሐዲሳትን ከሚቀጽሉ፣ ከብሉይ ትርጓሜ መምህራን ከአባ ገብረ ኢየሱስ፣ ከአባ ወልደ ማርያም፣ ከመምህር ጽጌ አንዳንድ ጉባኤ እየተማሩ መጻሕፍተ ብሉያትን ፣ ወንበር ዘርግተው ለማስተማር ባያበቃቸውም እንኳ ፣ ለራሳቸው ያህል አጥንተዋል::

ወደ እንጦጦ ማርያም እየተመላለሱም ፣ ከጎንደሩ ሊቅ ከመዝሙር ካሳ ከመጻሕፍተ ሊቃውንት ክፍል የሚመደቡትን፣ የፍትሐ ነገሥትንና የቁርሎስን ትርጓሜ በአጭር ጊዜ ውስጥ አጠናቀዋል::

ትጉሑና ታታሪው ኀሩይ እንጦጦ ራጉኤል ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ጊዜ ሥራ አልፈቱም ፤ በዲቁና ያገለግላሉ ፤ጽሕፈት በማወቃቸውም በወር አንዳንድ ብር እየተከፈላቸው ለስለት የሚገባውንና የሚወጣውን (ዘገብአና ዘወጽዓ) ይጽፉ ነበር:: በዚያን ጊዜ አንድ ብር እንዲህ እንደ ዛሬው ቀላል ገንዘብ አልነበረም- ብዙ ሥራ ይሠራል፤ ከላይ ከታች አቡጀዲ ያለብሳል::

በደብረ ኃይልም በመንበረ ፀሐይም የሚከታተሉትን ትምህርት እስከዚህ ካደረሱ በኋላ እዚያ በቆዩበት ጊዜ በወር 5 ብር (በኋላ ጊዜ እስከ ሰባት ብር ደርሰው ነበር ) እየተከፈላቸው በድብትርና አገልግለዋል:: በዚህም ላይ ቀደም ሲል በየወሩ የሚሰፈርላቸው አንዳንድ ዳውላ እህል አለ:: ለየባለ ጉዳዩ እየጻፉም የሚያገኙት ገቢ ስላለ ችግር አልነበረባቸውም::

ኀሩይ የማይሞክሩት፣ ሞክረውም እዳር ሳያደርሱት የሚቀር አንድም ነገር የለም::

እዚያው እመምህራቸው የኔታ ወልደ ጊዮርጊስ ግቢ ግንበኛም ፣ አናጢም፣ ሣር ከዳኝም ሆነው ሁለት ሦስት ሰው የምታዳብል ጎጆ ለራሳቸው ቀልሰዋል - ለጥሞና ጊዜና ለግል ጸሎት ትሆነኝ ብለው ::

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥቱ ዋና ሰው ብቻ ሳይሆኑ፣ የታላቁ የእንጦጦ ራጉኤልም አለቃ ስለ ነበሩ፣ የኀሩይን ችሎታ፣ ንቃት ትጋታቸውን እንዲሁም የጠባያቸውን መልካምነት ተከታትለው በሚገባ ለማወቅ በመቻላቸው ፣ ነገ ትልቅ ቦታ የሚደርሱ ሰው መሆናቸውን በማመን በንጉሠ ነገሥቱ በዐፄ ሚኒልክም፣ በሌሎቹም ታላላቅ መኳንንት ዘንድ እንዲታወቁላቸው ሞገስም እንዲያገኙ፣ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል:: እዚህ ላይ አንድ ነገር ብጠቅስ ደስ ይለኛል::

የእንጦጦ ማርያም አለቃ መላከ ፀሐይ አፈ ወርቅ ለጉዳይ ከጸሐፌ ትእዛዝ ዘንድ ሲመጡ ኀሩይ እዚያው ነበሩ:: ጸሐፌ ትእዛዝም መላከ ፀሐይን " ይህን ልጅ ታውቀዋለህ?" ብለው ሲጠይቃቸው " ያ በሐዲስ ትርጓሜ ችሎታው የሚወራለት ይህ ትንሽ ልጅ ነው እንዴ ?"ሲሉ ይመልሱላቸዋል:: በዚህ ጊዜ ጸሐፌ ትእዛዝ፣ " የምን ትንሽ ልጅ ትለዋለህ ?

ሰላም እብል ለጊዮርጊስ ቅዱሱ፣
ወኀሩይ አንተ እምንእሱ ::

በለው እንጂ" በማለት የልጅ አዋቂ፣ የትንሽ ትልቅ መሆናቸውን መጽሐፍ ጠቅሰው አፋቸውን አስይዘዋቸዋል::

ኀሩይ ዕድሜያቸው እየጨመረ ሲሄድ በትዳር መጠመድ ፈለጉ:: ስለዚህም በ25 ዓመታቸው ፣ የ16 ዓመትዋን ቆንጆ (ልጃ ረገድ) ወ/ሮ ሐመረ እሸቴን ግንቦት 17 ቀን 1895 ዓ.ም. በሕግ አገቡ:: ሐመረ ማለትም ፣ ኀሩይ በርጋ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በዜማቸው ከአደነቁአቸው የራጉኤል ካህናት አንዱ የሆኑት ፣ የአቶ ማንደ



www.ethiopianorthodox.org

ረ እህት ልጅ ናቸው ። ከሁለቱ ጋብቻም አራት ሴትና ሁለት ወንድ ልጆች ተገኝተዋል። ባልና ሚስት በሕይወት ሳሉ የልጅ ልጆች ለማየት ታድለዋል። የልጅ ልጆቻቸው እንዲሁም የልጅ ልጅ ልጆቻቸው ዛሬ በአዲስ አበባም በውጭም ይገኛሉ።

ምን ጊዜም ቢሆን፣ የዕውቀት ጥማታቸው የማይረካው ኅሩይ፣ በዚህ በቤተ ክህነቱ ትምህርት ብቻ ተወስነው ለመቅረት አልፈለጉም ፤ ስለዚህም ከእንጦጦ ወደ ሰዊዲሽ ሚሺን ትምህርት ቤት በቀን በቀን እየተመላለሱ፣ ለስድስት ወር ያህል አንዳንድ ሰዓት እንደተማሩ፣ ነገረ - ሠሪዎች "ኅሩይ ሊኮተልክ ነው " ብለው ስላስወሩባቸው ፣ ክፉኛ አዝነው ትምህርቱን አቆሙ። ይሁን እንጂ ፣ በግል ማጥናቱን አልተውም- በራሳቸው ጥረት ቀጠሉበት።

እንደ ገና ደግሞ ከአንዱ ግብፃዊ ተጠግተው ዐረቢኛ ለመማር ጀመሩ። አሁን ደሞ፣ " ይኼ ሰው ሊሰልም ነው" የሚል ሐሜት ተናፈሰ ፤ ተውት።

ከዚህ በኋላ ደግሞ የከብት ሐኪሞች ለእርዳታ ከፈረንሳይ ሀገር ይመጣሉ። ታዲያ ትምህርት የሚወድ ሰው ይፈለግ ተባለና ተመርጠው በወር የዐሥር ብር ደመወዝ ተቆረጠላቸው ። ከእንጦጦ - ጉለሌ በእግር መመላለሱ ከባድ ነገር ስለ ሆነባቸው መኖሪያቸውን ወደ ጉለሌ አዛወሩ። ከእነዚህም ፈረንጆች የፈረንሳይኛ ቋንቋ ተማሩ ፤ በሥራው ግን ስላልተደሰቱበት እነርሱ ከሄዱ በኋላ አልገፉበትም።

የእጅ ጽሕፈቱም ሙያ፣ የውጭ አገር ቋንቋ ለማወቅ በግል የሚያደርጉትም ጥረት ተደማምሮ፣ ከፈረንጆች ጋር ለሚደረግ ግንኙነት ሁሉ የኅሩይ ተፈላጊነት እየጐላ መጣ። በ1903 ዓ.ም. በእንግሊዝ ንጉሥ ጆርጅ አምስተኛ የንግሥና በዓል ላይ ለመገኘት በራስ ካሳ ኃይሉ የሚመራ ቡድን እንዲሄድ ሲወሰን፣ ኅሩይም በጸሐፊነት አብረው እንዲሄዱ ተደረገ።

ሎንዶን በበዓለ ንግሡ ላይ ከተገኙ በኋላ፣ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲን፣ ፓሪስንና ሮምን ፣ እስክንድርያን፣ ካይሮንና ኢየሩሳሌምን ለመጐብኘት ቻሉ። ይኼም ጉብኝት በጊዜው የሠለጠነው ዓለም የደረሰበትን ዕድገት እንዲያዩ ስላበቃቸው ፣ ሀገራቸው እዚህ ደረጃ የምትደርሰው መቼ ይሆን ? የሚለው ሐሳብና ጭንቀት ፣ ዕድሜ ልካቸውን ዕረፍት ሲነሣቸው ኖሯል።

ከአውሮፓው ጉዞ እንደተመለሱም፣ ያን ጊዜ የንግድና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኋላም የልጅ ኢያሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት፣ ጠንካራው ሰው ቢትወደድ ኀይለ ጊዮርጊስ፣ የኅሩይን ብልኀነትና ጠንቃቃነት፣ ትጋት ፣ ብርታትና ሥራ ወዳድነት ቀደም አድርገው ያውቁ ስለ ነበር፣ በአዲስ መልክ ላቋቋሙት ለከንቲባው ጽ/ቤት አምስት የውጭ ሀገር ሰዎች ቀጥረው የዲሬክተርነቱ ቦታ የኅሩይ ሆነ ፤ የወር ደመወዛቸውም ወደ ሀምሳ ብር ከፍ አለ። በኋላም የከንቲባነቱን ቦታ ተረከቡ ። በነገራችን ላይ፣ ፈረንጆች ሚዩኒሲፖሊቲ ለሚሉት የከተማ አስተዳደር መ/ቤት "ማዘጋጃ ቤት" የሚለውን ስም የፈጠሩት ኅሩይ መሆናቸውን ዛሬ ስንት ሰው ያውቃል ? የከንቲባውን ጽ/ቤት በአዲስ መልክ ያደራጁት ፣ የከተማ ቦታ ካርታና ቀረጥን ወዘተ ለአዲስ አበባ ሕዝብ በመጀመሪያ ያስተዋወቁት ኅሩይ መሆናቸውንስ ዛሬ - ዛሬ የሚያውቅ ስንት ሰው አለ ?

ዐልጋ ከተዛወረ በኋላ ፣ ኅሩይ የዕድላቸው ኮከብ ይበልጥ የበራ ሆነ ። በተለያዩም ጊዜያት በመልክተኝነትም፣ ለሥራም ፣ ለሕክምናም፣ ለሌላ ሌላም ጉዳይ እየተላኩ ወደ አውሮፓም፣ ወደ አሜሪካም ፣ ወደ እስያ፣ (ሩቅ ምሥራቅ) እስከ ጃፓን ድረስ በመርከብ ተጉዘዋል። ከዚህም ጉዞአቸው - ለሀገራቸው ዕድገትና ልማት የሚበጅ ከፍ ያለ ልምድ (ኤክስፒሪያንስ) እንዳገኙ ግልጽ ነው።

ታላቁ ሰው ኅሩይ በ1914 ዓ.ም. ልክ በ44 ዓመታቸው ብላታ ተብለው በልዩ ለቆመው ፍርድ ቤት ዋና ዳኛ ሆኑ፣ ፍትሐ ነገሥቱን የተማሩት ስለሆነም ከመደነቅና ከመመስገን ጋር ኀላፊነታቸውን በሚገባ ሊወጡ ችለዋል።

በ1919 ዓ.ም. የልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ልዩ አማካሪ፣

በ1920 ዓ.ም. ብላቴን ጌታ ተብለው ፣የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ሆኑ።

ዕውቀታቸው፣ ችሎታቸው ተመዝኖ፣ ታማኝነታቸው፣ ትጋት ብርታታቸው በሚገባ ታውቆ ለቦታው ብቁ ሰው ሆነው ስለተገኙ፣ ሁነኛ ሰው አጥተው ለት፣ ራሳቸው ልዑል አልጋ ወራሹ ራስ ተፈሪ ደርበው ይዘውት የነበረውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት በ1923 ዓ.ም. ተሾሙት።

ይህ ጊዜ ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር ውስጥ ውስጡን ዝግጅት የምታደርግበት ወቅት ስለሆነ፣ ውስብስብና ጥልፍልፍ የነበረውን የፖለቲካ ጨዋታ ከዋናው መድረክ አናት ላይ ሆነው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በሚገባ ተጫውተውታል።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ከሥራ ውጭ ያለውን የዕረፍት ጊዜ አቸውን በመዝናናት የሚያሳልፉ ሰው አልነበሩም። መጻሕፍትን ያነባሉ ፤ ይመረምራሉ፤ ከታላላቁ ምሁራን ጋር ይነጋገራሉ፣ ይወያያሉ ፤ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ ጽሑፎችን ያዘጋጃሉ እንጂ ፣ እንዲሁ በከንቱ የምታልፍ የአንዲት ደቂቃ ጊዜ አልነበረቻቸውም።

ከዚሁ የተነሣም፣ አንብቡኝ ፣ አንብቡኝ በሚል በጥሩ አማርኛ ወደ 30 የሚጠጉ መጻሕፍት ደርሰዋል።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ዋናው ትምህርታቸው የቤተ ክህነት ስለሆነ፣ መጻሕፍቶቻቸው ብዙውን ጊዜ የሚያተኵሩት በሃይማኖትና በሥነ ምግባር ላይ ነው።

እንደ ማር እንደ ወተት የሚጣፍጥ ትምህርትዋን እየጠባች፣ እየጋተች ያሳደገቻቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፊትዋ ላይ አንዳች ጉድፍ፣ አንዳች ቱሻሽ ነገር እንዲያዩባት አይፈልጉም ፤ ይወዱአታል፤ ይጨነቁላታል። ከሕጉችዋ፣ ከሥርዓቶችዋ አንዲትዋ ጸጉር እንድትነካ አይፈልጉም። ከዚህ የተነሣም ከቀን በኋላ ሠርጎ ገብቶ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የተንሰራፋውን አጉል ልማድ ሁሉ ለማስቀረት ሲሉ፤ "አዲስ ዓለም የቅችና የደግ አድራጊዎች መኖሪያ" እና "የልብ ሐሳብ ፤ የብርሃኔና የጽዮን ሞገሳ ጋብቻ " የተሰኙ ሁለት መጻሕፍት ደርሰዋል።

አዲስ ዓለም በተባለው መጽሐፋቸው ላይ በፈጠሩአቸው ተቃራኒ ገጸ ባሕርያት በዐወቀና በመምሬ ሰባጋዲስ አማካይነት መጠበቅ፣ መሆን፣ መደረግ ያለባቸውን መልካም ነገሮች፣ መቅረት ፣ መሻሻል ፣ መለወጥ ያለባቸውን "በስሕተት የገቡ ክፉ ልማዶች" በግልጽ አስቀምጠዋል ፤ በቁጥር ዐሥር ናቸው - እንደ ዐሠርቱ ቃላት ። ከነዚህም አንዱና ዋናው "ተዝካር በሚያስከር መጠጥ መውጣቱ ቀርቶ በገንዘብ ይሁን "የሚል ነው። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ከተዝካር ቤት ሰክረው እየወጡ በየመንገዱ ላይ ሲንገዳገዱ ያዩአቸው የውጭ አገር ሰዎች ፎቶ ግራፍ በማንሳት ወደ አገራቸው እየላኩ በሣቂያ፣ መሣለቂያ ማድረጋቸው ካህናቱን የሚያዋርድ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚያስድብ መሆኑ ያስቆጫቸው፣ ያሳዝናቸው ነበርና ነው። በወቅቱ ግን ሰሚ አላገኘም ነበር። ይሁን እንጂ ምን ጊዜም የሐሳባቸው ደጋፊ የሆኑት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጃቸው ልዕልት ዘነበ ወርቅ ባረፉ ጊዜ ፣ ምክንያት ስለ ተገኘ፣ ይህንኑ የክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ሐሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚደግፍ ዓዋጅ በሚያዝያ 1925 ዓ.ም. አውጥተዋል። ታዲያ ጥቅማችን ተነካ ከሚሉ ወገኖች:-

ንጉሡ ተፈሪ ጳጳሱ ኅሩይ፣

የሃይማኖት ነገር ቀርቶ የለም ወይ ፤

የሚለው ግጥም የተገጠመውና የተናፈሰው በዚህ ጊዜ ነበር፤ -ስም ለማጥፋት ብቻ ሲባል። ዛሬ ግን ይኸው ፣ ጥቅምና ጉዳቱ ታውቆ በምግብ በመጠጥ የሚወጣው ተዝካር በገንዘብ ተለውጦ ሲሠራበት ይታያል። ያን ጊዜ እሳቸው አጥብቀው የኮነኑአቸውን ሌሎች ሌሎች አጉል ልማዶች ዛሬ ራስዋ ቤተ ክርስቲያኒቱ በውስጥ መመሪያም በግልጽም እን



www.ethiopianorthodox.org

ዲሻሻሉ በማድረግ ላይ ትገኛለች - ጊዜው ደርሶ::

መጻሕፍቶቻቸውን በተለይ ጎህ ጽባሕን፣ ጥሩ ምንጭን ፣ ሀገረ ጃፓንን ፣ ወዳጄ ልቤን፣ ደስታና ክብርን በጥምና ያነበበ ሰው ፣ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የራሳቸውን ሃይማኖት አጥባቂ የሌሎቹንም አክባሪ መሆናቸውን በቀላሉ ሊረዳ ይችላል:: ምናልባትም ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ "ሀገር የጋራ፣ ሃይማኖት የግል ነው " የሚለውን ሰፋ ያለ አመለካከት እንዲከተሉ የመከሩ እርሳቸው ሳይሆኑ እንደማይቀሩ መገመት ይቻላል::

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የጻፉአቸው መጻሕፍት በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን፤ በዓለም ዙሪያም ከፍ ያለ ዝናን ስላተረፉላቸው፣ "ዲቼ ሞርጌንሌንደሼ ጌዜልሻፍት" የተባለ የጀርመን ድርጅት (Society) የአማርኛና የግእዝ ቋንቋ ሊቅነታቸውን በማረጋገጥ ጥቂት ፣ ግና ምርጥ ለሆኑት የዓለም ታላላቅ ሊቃውንት ብቻ የሚገባውን የምስክር ወረቀት ለኒህ ታላቅ ሰው ሰጥቶ ፣ የክብር አባሉ አድርጎአቸዋል:: ሥራዎቻቸውንና የዲፕሎማታክ ችሎታቸውን በተመለከተም በየጊዜው ከተለያዩ መንግሥታት የተለያዩ ከፍተኛ ኒሻኖች ተሸልመዋል::

ሥራዎቻቸው በሌላው ዓለም የቱን ያህል የሚወደዱ፣ የሚፈለጉ መሆናቸውን በድጋሚ ለማሳየትም" ማኅደረ ብርሃን፣ ሀገረ ጃፓን "የተባለው ባለ ትልቅ ጥራዝ መጽሐፋቸው ወደ ጃፓንኛ ቋንቋ መመለሱን በተጨማሪ እዚህ ላይ መጥቀሱ ተገቢ ይመስለኛል-በዚያኑ ጊዜ::

ያን ጊዜ ይህን ክብር ያስጡአቸው መጻሕፍቶቻቸው ዛሬም በውጭው ዓለም ሥራ አልፈቱም:: በሥነ ጽሑፍ ሊቃውንት ይጠናሉ፣ ይመረመራሉ ፤ ይፈተሻሉ ፤ በየጊዜውም በየታላላቁ ስብሰባና መድረክ ላይ ጥናታዊ ጽሑፎች ይቀርቡባቸዋል:: ወጣቱ ትውልዳችን ግን ስለክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና ስለ ሥራዎቻቸው እስከዚህ ምን የሚያውቀው አለ ?

ለሀገራቸውና ለወገናቸው በፖለቲካውም መድረክ በዲፕሎማሲውም መስክ፣ በሥነ ጽሑፉም ዓለም ከፍ ያለ አገልግሎት ያበረከቱት እኒህ ታላቅ ሰው፣ ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሥርዓተ ቀብሩ ላይ:-

ብልኅነቱንና ትጋቱን ለመልካም ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ስላደረጋቸው፣ በመንግሥታችን ሥራ ለመመረጥና ወደ ታላቁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ማዕረግ ለመድረስ በቃ:: በየጊዜውም የጻፋቸው / ከፍተኛ ባሕርይውን የሚገልጹ መጻሕፍቶቹ ፣ ይልቁንም በቤተ ክህነትና በታሪክ ዕውቀት በዓለም ሊቃውንትም ዘንድ የታወቀና የተከበረ አደረጉት:: ለም ታውቂት ሰው ከታሪኩ ከዚህ የበለጠ ልንነግራችሁ የሚያስፈልግ አይመስለንም::



በአጭሩ ከጠባዩ ትልቅነት የሚሰማኝን ለመናገር ሳስብ፣ ጊዜውን ሁሉ ቁም ነገር በመሥራት ማሳለፉ፣ ከራሱ ይልቅ የተቸገሩትን ሰዎች ለመርዳት መጣሩ፣ እውነ ትንና ፍርድንም ማክበሩና በአገር ፍቅር መቃጠሉ ትዝ ይለኛል:: አገ ልጋዬና ወዳጄ ኅሩይ፣ በተቻለህ ስለ አገርህ ሥራህን ፈጽመህ በምትሰ ናበትበት ጊዜ ፣ ታላቅ ነህ ሳልልህ ብቀር ሥራዎችህ ቀድመውኝ ይና ገራሉ::»

የፕሮቶኮልን ዳር ድንበር የጣሰ፣ ከጥልቅ የስሜት ሕዋሳት ጉድጓድ ፈንቅሎ የወጣ እውነተኛ የምስክርነት ቃል ::

" ውብ በሆኑ ቃላት የተገለጸው ፣ይኼ ልብ የሚነካ ንግግር፣ ከታወቀው ከተደነቀው ከሊንከልን የጌትስበርግ ወርቅማ ንግግር በምን ያንሳል ?

ጃንሆይ፣ እቴጌም ልዑላን ልዕልታት ልጆቻቸውም፣ ቀድመው ባረፉ ጊዜ እንደዚሁ ንግግር አድርገዋል ፤ እነዚያ ንግግሮች ከዚህኛው ጋር ሲነጻጸሩ ግን ፣ ምንና ምን ??

ብቻ ማንም ይበል ማን ፣ ስለ ታላቁ ሰው ኅሩይ ማንነት ከዚህ የሚበልጥ ምስክርነት ሊኖር አይችልም::

ቦታና ጊዜ አልፈቅድ ስላለ ብቻ፣ እንግዲህ የተነሣሁበትን ጉዳይ እዚህ ላይ መግታቱ ተገቢ ይመስለኛል -እንዲሁ ባጭሩ:: ይሁን እንጂ፣ ከፍ ብዬ የጠቀስኩትን መሠረታዊ ቁም ነገር ግን እንዲሁ ዝም ብዬ ማለፍ አልፈልግም:: አዎን አሁንም እዚህ ላይ እንደ ገና ልድገመውና ወጣቱ ትውልድ፣ ስለ እርሳቸውም ሆነ ስለ ሥራ ዎቻቸው ምን የሚያውቀው አለ ?- ታዲያ በቤተ ሰብ በኩልስ ምን የተደረገ፣ የታሰበ ነገር አለ?- ለማሳወቅ::

ለሀገርና ለወገን፣ ይኼን ያህል አገልግሎት በቅንነት ላበረከቱት ለእኒህ ታላቅ ምሁር፣ዲፕሎማት፣ "የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ አባት " በመን ግሥትስ በኩል ምን ተደርጉአል ? ምንስ ታስቦአል ?

በብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት የምትገኝ አንዲት የንባብ ክፍል ብቻ ለመታሰቢያነታቸው በእርግጥ በቂ ናት ? ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ፣እኒህ ስመ ጥር ደራሲና ሥራዎቻቸው አሁን ማ ይሙት ከፑሽኪንና ከሥራዎቹ ያንሳሉ ? በእርግጥ ፑሽኪንም የሥነ ጽሑፍ ሰው ነው - ታላቅ ! ይኼን መካድ አይቻልም:: ኢትዮጵያዊ ደም ስላለው - በአንድ ወገኑ ቢሆንም እንኳ - ሥጋችን ነውና ፣ ስሙ በመጠራቱ ደስ ይለናል ፤ እናከብርዋለን ፤ እናደንቀዋለን - እኛም እንደሌሎቹ፤ እንደኛነታችንም::

ግና በሥራዎቹ ራሱ ታወቀ ፣ ሩስያን አስታወቀ አስተዋወቀ እንጂ ፣ በሥነ ጽሑፍም ሆነ በሌላ -አሁን ማይሙት - ከታላቁ ኅሩይ የበለጠ ለኢትዮጵያ የሠራው፣ ኢትዮጵያንና ሕዝብዋን የጠቀመ ምን ነገር አለ?

እውነት እውነትዋን ብቻ እንነጋገር ከተባለ - በምንም ይሁን በምን - ከፑሽኪንና ከኅሩይ ለእኛ ማ ይቀርበናል? ማንስ ይበልጥብናል? ኅሩይን አናውቃቸውም ? ወይስ ልናውቃቸው፣ልናሳውቃቸው ስ አንፈልግም? ነገ ታሪክ አይወቅሰንም ? እትዝብት ላይስ አንወድቅም ? ይህ እንዲሆን አልፈልግም::

አሁን፣ ይኼን እንኳ፣ እዚህ ላይ ያነሣሁት፣ ለሌላ ሳይሆን - በዚህ አጋጣሚ እንዲሁ ለማሳሰብ ያህል ብቻ ነው - ቤተ ሰብንም፣ ጉዳዩ የሚመለከተውንም የመንግሥት አካል - ይበልጥ እንዲታሰብበት፣ ልዩ ትኩረትም እንዲሰጠው::

❋ ❋ ❋



www.ethiopianorthodox.org

# የአፄ ዳዊት ፍልፍል ዋሻ

ጥንታዊና ድንቅ የታሪክ ቅርሶች ካሏቸው ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ በመሆን ትጠቀሣለች:: በወሎ ላሊበላ የሚገኙና ከድንጋይ ተፈልፍለው የተሰሩ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት፣ ከአንድ ወጥ ድንጋይ የተቀረፁ የአክሱም ሐውልቶች፣ በጐንደር የሚገኙ ቤተ መንግሥቶች፣ በጣና ሐይቅ ደሴት የሚገኙ ጥንታዊ ገዳማት፣ በአክሱም የሃ ጥንታዊ የሙክራብ ህንፃ፣ በድንጋይ ላይ የተቀረፁ ዜና መዋዕሎች፣ የዋሻና የቤተክርስቲያን ውስጥ ስዕሎች እና የመሳሰሉት በታሪክ መረጃነታቸው ከምንጠቅሳቸው ብርቅ ቅርሶቻችን ጥቂቶቹ ናቸው:: እነዚህ የቀደምት ታሪካችን ሁለተናዊ ገጽታዎች አንጸባራቂ በመሆናቸው የማንነታችን መገለጫ ተደርገው ይወሰዳሉ::

በእርግጥ በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ ቅርሶች በታሪክ ምስክርነታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብቶች ብቻም ሳይሆኑ የመላው የሰው ልጅ ቅርስም ተብለው በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ተመዝገበው ይገኛሉ:: እነዚህ ጥንታዊ የሆኑ ሰው ሰራሽ ቅርሶች ተጠብቀው በመገኘታቸው የሚሰጡት አገልግሎት ከፍ ያለ ነው:: በቱሪስት መስህብነታቸውም ለሀገራችን ጠቃም ያለ የገቢ ምንጭ በማስገኘት ረገድም ጉልህ ሚና ይጫወታሉ:: በዚህ መጽሔት ለጭስ አልባው የቱሪዝም እድገት የራሱ ድርሻ አለው ብለን ያመንበትን በእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል የሚገኘውንና ለዘመናት አስታዋሽ በማጣት ለባለቤቱ ባእድ የሆነውን የአፄ ዳዊትን ፍልፍል ዋሻ ልናስተዋውቃችሁ ወደናልና አብረን በምናብ ጉዞ እናድርግ:-

ይህ ጥንታዊ ዋሻ ተፈልፍሎ የተሰራው በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት በ1375 ዓ.ም ገደማ ነው:: በዘመኑ የኢትዮያጵያ ንጉሥ ነገሥት የነበሩት አፄ ዳዊት የመናገሻ ከተማቸው እንጦጦ እንደነበረና ቤተ መንግሥታቸውንም በዚሁ ቦታ ላይ አስርተው ይኖሩ እንደነበር በታሪክ ተመዝግቧል:: ንጉሡ ይህንኑ ዋሻ አሠርተውት የነበረው ለወርቅ ማስቀመጫ ግምጃ ቤትነት ነበር:: በርካታ የታሪክ ምሁራንና የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች እንደጻፉትና በተጨባጭም እንደሚታየው የጥንት ኢትዮጵያውያን አለት ፈልፍለውና ተራራ ቦርቡረው በሚደንቅ ጥበብ፣ አብያተ ክርስቲያናትንና ቤተመንግስቶችን የመሥራት ባህላቸው የቆየ እንደሆነ በመሥኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ምሥክርነታቸውን ሰጥተዋል:: የዚሁ ጥበብ ባለድርሻ የሆነው የአፄ ዳዊት ፍልፍል ዋሻ የቀድሞ አገልግሎቱ ግምጃ ቤት ቢሆንም በኋላ ግን ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ውሎ ነበር::

አፄ ምኒልክ የአባቶቻቸውን ከተማ በመፈለግ ሲደክሙ ቆይተው በመጨረሻ ሱሉልታ ላይ ሆነው የአፄ ዳዊት ከተማ የነበረችውን እንጦጦ ፍራሹ መገኘቱ ሲነገራቸው ደስ ብሏቸው ወዲያውኑ ፈጥነው መጥተው አዩት ሲሉ ፀሐፊ ትዕዛዝ ገ/ሥላሴ:- «ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ» በተባለው መጽሐፋቸው ይገልጻሉ:: ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ወጥተው አካባቢውን ሲቃኙ በማያጠራጥር ምልክትነት ካገኟቸው መረጃዎች መካከል አንዱ ይህ የአፄ ዳዊት ዋሻ ነበር:: ቦታው ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ የተገኘ በመሆኑ አራዊት ሰልጥኖበት፣ ዳዋ ውጦትና ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳልነበረበት ፀሐፌ ትዕዛዝ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ውስጥ አስፍረውታል::

ንጉሡ አጼ ምኒልክ የአባቶቻቸውን ሕያው የታሪክ ቅርስ አሻራ ባዩ ጊዜ እጅግ ተደሰቱ:: የአፄ ዳዊት ከተማ የነበረውን እውነተኛውን የእንጦጦ ከተማ ካገኘነው የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ቢሆን ነው፣ በእኛ ጊዜ የገለጠው በማለት የቅዱስ ራጉኤልን ቤተ ክርስቲያን ህንጻ ሥራ አስጀመሩ፣ የቤተ ክርስቲያኑም ሥራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሊቀ መላዕክት ቅዱስ ራጉኤል ጽላት በዚሁ ዋሻ ውስጥ እንዲቆይ ንጉሡ አፄ ምኒልክ መወሰናቸውን የፀሐፌ ትዕዛዝ ገ/ሥላሴ መጽሐፍ ያትታል:: ይህ ፍልፍል ዋሻ ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ቅኔ ማኅሌት፣ መቅደስና የሴቶች መቆሚያ ክፍሎች ናቸው:: አንዳንድ ዋሻውን ለመጎብኘት የመጡ የውጭ ሀገር ጐብኚዎች በጥንታዊነቱ በአስደናቂነቱ በሀገራችን በተለይም በሰሜኑ ክፍል ከሚገኙ ከአለት ተፈልፍለው ከተሰሩ አብያት ክርስቲየናት መካከል አንዱ እንደሆነ ሲናገሩ አንዳንድ የምህንድስና ባለሙያዎች ደግሞ መጠኑና ውስብስብነቱ አነስተኛ ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ውስጥ በብቸኝነት መገኘቱ ምናልባትም የዚህ አይነቱ ጥበብ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ሊገኝ እንደሚችልና ለወደፊት ለምርምርና ለጥናት በርከፋች እንደሚሆን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል:: ዋሻው ከ600 ዓመታት በላይ ታሪክ ያለው በመሆኑ በከፍተኛ ጥንቃቄ በዓለም አቀፍ ቅርስነት መጠበቅ የሚገባውና ለታሪክ አጥኚዎችና ለቅርስ ተመራማሪዎች ክፍት በማድረግ ለአካባቢውና ለሀገሪቱ የቱሪዝም እድገት ከፍተኛ የሆነ ሚና ሊኖረው እንደሚችል ብዙዎች አስተያየታቸውን ይሰጣሉ:: ምን ያህሎቻችን የከተማዋ ነዋሪዎች ይሄን ዋሻ እንደምናውቀው ምስክርነት ለመስጠት ያዳግታል፣ ይህ ባለታሪክ ዋሻ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ውኃ እየሸረሸረው ሊፈርስ ተቃርቦ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው:: በአካባቢው የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ለቅርስ ግንዛቤ ካላቸው እውቀት አናሣ መሆን የተነሳ ይሄ ጥንታዊ ዋሻ በአንድ ወቅትም የንፍሮ መቀቀያ ማድቤት ተደርጐ እንደነበር ተገንዝበናል::

በ1993 ዓ.ም አባ ፈጠነ የተባሉ መናኝ መነኩሴ ወደ ደብሩ መጥተው በወቅቱ አጋጥሟቸው ከነበረው ህመም ከተፈወሱ በኋላ በሞት አፋፍ ላይ ይገኝ የነበረውን ይህንን ዋሻ ለመታደግ እንቅስቃሴ ጀመሩ:: ምዕምናንን በማስተባበርና ዋሻውን እንዲጐበኙት በማድረግ በሰበሰቡት ገንዘብ የዋሻዋን አናት በአርማታ በማስደፈንና ወደዋሻው ውስጥ እየሰረገ ይገባ የነበረውን ውኃ በማስወገድ ይሄን ጥንታዊ ዋሻ ከመፍረስ ለማዳን ቻሉ:: በዚህም ዋሻው ጥንታዊ ቅርስነቱን ጠብቆ ለቱሪስቶችና ለጐብኚዎች ምቹ እንዲሆን የተቻለቸውን ጥረት በማድረግ ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል:: እኚህ መነኩሴ የቅዱስ ራጉኤልን ጥንታዊ ስዕሎች ከወደቁበት በማስባሰብ ዋሻው ውስጥ በመለጠፍ የዋሻውን ውበትና ታሪካዊነት በማጉላት ያደረጉት ጥረት ዋሻው በአካባቢው ባለው ቅዝቃዜና ርጥበት የተነሳ እየወረዛ በስዕሎቹ ላይ ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ ባለሙያ ተገኝቶ መፍትኄ እስኪገኝለት ድረስ ዋሻውን በመንፈሳዊ ሥዕሎች የማስዋቡ ሥራ እንዲቋረጥ ተደርጓል::


ይህ ታሪካዊ ዋሻ በአዲስ አበባ ከተማችን አፍንጫ ሥር የሚገኝ በርካታ የውጭ ቱሪስቶች የሚጐበኙት ድንቅ ሥፍራ በመሆኑ ለዚህ ጥንታዊ ቅርስ፣ በቤተክርስቲያኑ ለሚገኙ በርካታ ጥንታዊ፣ ታሪካዊና መንፈሳዊ ቅርሶቻችን ላይ እየደረሰ ላለው ብልሽት በተለይም የቅርስ አጠባበቅ ኤክስፐርቶች ሙያዊ ድጋፍ፣ የመንግስትና የህዝብ ትኩረት ወሳኝ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን:: የሁላችን መመኪያና አለኝታ፣ ለሃገራችንም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ሊያስገኝ የሚችለውን የአባቶቻችንን ቅርስ ለበለጠ አደጋ ከመጋለጣቸው በፊት ቆም ብለን ልናስብ ይገባናል::



www.ethiopianorthodox.org

# መንትዮች


በታሪክ የጉዞ ሂደት ውስጥ በአንድ ትውልድ ተጸንሰው ረጅሙን ጉዳና በአብሮነት የተጓዙ ጥቂቶች ናቸው:: ለዚህ ተጨባጭ ምሣሌ አድርገን



ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም

የምናነሳቸው እንጦጦ የሀገራችን ማዕከላዊ ከተማ በነበረችበት በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን መንግሥት ተሠርተው የነበሩት አብያተ ክርስትያናት እንጦጦ ማርያምና እንጦጦ ራጉኤል ብቻ አልነበሩም:: በዘመናት ሂደት ጉዞአቸውን ጨርሰው የከሰሙ፣ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ከነበሩበት ቦታ ለቀው በሌሎች ሥፍራዎች የተተከሉ ይገኙባቸዋል:: አጼ ምኒልክ በእንጦጦ ላይ ከተከሏቸው አብያተ ክርስትያናት መካከል ቅዱስ ዑራኤል፣ ቅዱስ ኤልያስና ሌሎችም ነበሩ:: የቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስትያን አርጅቶ በመፍረሱ ምክንያት በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ አሁን በሚገኝበት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንዲሠራ ተደርጓል:: የቅዱስ ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን በተመሣሣይ ሁኔታ በመፍረሱና በወቅቱ ተከስቶ በነበረው ረሀብ ካህናቱ በማለቃቸው ከቅዱስ ራጉኤል ጋር እንዲዳበል ተደረገ:: እንጦጦ ማርያምና እንጦጦ ራጉኤል በዚያው ዘመን የተተከሉ ሲሆን የታሪክ ሂደታቸውን ሳይለቁ አብረው የተጓዙና የእንጦጦን የታሪክ ቦታነት ለማሣወቅ በህያው አስረጂነት እስከዛሬ የሚገኙት እነርሱ ብቻ ናቸው::

አጼ ምኒልክና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ሰምና ወርቅ ሆነው ሀገራችንን በመመካከር ሲመሩና ሲያስተዳድሩ እንደነበር በርካታ የታሪክ ምሁራን ጽፈዋል:: ይልቁንም እቴጌ ጣይቱ በተፈጥሮ ብልህነታቸው በታሳቅ ታሪካዊ ክንዋኔዎች ውስጥ



ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ራጉኤል

ጉልህ ሚና እንደነበራቸው ተረጋግጧል:: እንጦጦ ማርያምና እንጦጦ ራጉኤልም በዘመኑ የነበረውን ታሪክ ለመመስከር በቋሚ ቅርስነት ለዚህ ትውልድ የደረሱ የምኒልክና የጣይቱ ማስታወሻዎች ናቸው::

ሁ ለ ቱ አ ብ ያ ተ ክርስትያናት በጉውንና ክፉውን ዘመን እኩል በመታዘብ ጊዜ የሚወስደውንና የሚያመጣውን ውጣውረድ አብረው እየተጋሩ በማለፍ መጓዛቸው ብቻ ሳይሆን ክብርና ሞገሳቸው ገናና የነበረበት ወርቃማ ዘመን አልፎ እንጦጦ ከተማነቷ እየረገፈ በምትኩ አዲስ አበባ ሲያብብ የነበረው የተሟሟቀ ሁኔታ እየቀዘቀዘ አጀቡ ሲቀል የተከሰተውን ችግር ሁሉ አብረው በመቋቋም አሳልፈውታል:: ሁለቱን አብያተ ክርስትያናት መንትዮች ያሰኛቸውም ከአንድ ትውልድ አብራክ መፈጠራቸው ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የተከሰተውን የታሪክ ማዕበል ሁሉ ተቋቋመው በአንድነት መዝለቃቸው ጭምር ነው::

የሁለቱ አብያተ ክርስትያናት መስራች ትውልዶች አድባራቱ የታሪክ ምስክር ሆነው ስማቸውን እንዲያስጠሩ በጽኑ መሠረት ላይ ተክለውና ቅርሶቻቸውን ሁሉ አውርሰው አልፈዋል:: ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያምን ከእንጦጦ ራጉኤል ልዩ የሚያደርጋት የቀድሞውን ትውልድ ታሪክ በህያውነት እያንፀባረቀች መገኘቷ ነው:: ቤተ ክርስትያኒቷ የተረከበቻቸውን ታሪካዊ ቅርሶች ጠብቃ እንኳንስ ወገንን የውጪውን ሰው ጭምር የምትማርክ ሆና መገኘቷ መስራቹ ትውልድ በሕይወተ ሥጋ እንደገና ተነስቶ ቢያያት በድርጊቱ መደነቁና መኩራቱ አያጠያይቅም፣ ከዚህ አንጻር የእንጦጦ ራጉኤልን ሁኔታ ስንቃኝ በዚህ መጽሔት ውስጥ በተደጋጋሚ ባጋጠሙት ችግሮች ምክንያት ታሪኩ በመናጋቱና ቅርሶቹ በመበታተናቸው ምክንያት እነዚያን እጹብ ድንቅ ታሪክ ሠርተው ያለፉትን አባቶች ብቻ ሳይሆን የዚህንም ትውልድ ልብ በሀዘን መውጋቱ አይቀሬ ነው::


www.ethiopianorthodox.org



ዳግማዊ ሃዬ ምኒልክ

ስናጤን በዚሁ ሁኔታ የተከሰተ ሰው ሠራሽ በደል እንደሆነ ለመገንዘብ አዳጋች አይደለም። ይህ ቤተ ክርስቲያን በነበረው ላይ እየተጨመ ረለት እንዲገዝ ቢደረግ ኖሮ የተፈጠሩት ችግሮች ሁሉ ባልተከሰቱና ዛሬ ቤተ ክርስትያኑን ለማቀናት የሚደረገው ድካም ሁሉ በቀረ ነበር።


እንጦጦ ማርያምና እንጦጦ ራጉኤል በ ረጅሙ የአብሮነት ጉዞአቸው ሂደት በርካታ አ ስደናቂና ስሜትን የሚነኩ ታሪካዊ ክንዋኔ ዎችን አስተናግደዋል። ታላላቅ በዓላትን በአንድነት ሲያከብሩ ኖረዋል። ዛሬም እያከበሩ ናቸው። ለዚህም ታሪካዊ መሠረት አለው። ይህንንም በተመለከተ ደግማዊ አጼ ምኒልክ ከጻፏቸው ደብዳቤዎች በአንዳኛው ላይ የተ ጠቀሰውን እንመልከት

ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ሁለቱ የአድባራት የቦታ ወሰን ሲካለሉ የተከሰተ ውን አስደናቂ ሁኔታ ነው። በማርያምና በራጉኤል መካከል ስላላው ቦታ ካህናቱ በወሰን ምክንያት ብዙ ጊዜ ይከራከሩ ነበር። በ1899 ዓ.ም በጥቅምት ወር ቦታው እንዲከለል ዳግማዊ ምኒልክ ስላዘዙ ሊጋ ባውና አጋፋሪው፣ አፈንጉሡና ሌሎችም መኳንንት በተገ ኙበት ክፍ ባለ ሥርዓት እንደሚከተለው ሆ ተከለለ።

*«የሊቀ ጳጳሱ የአቡነ ማቴዎስ አርዌ ብርት ተይዞ ቀሣውስትና ዲያቆናት ልብሰ ተ ክህኖ ለብሰው መስቀል ተሸክመው ከሥፍራው ላይ ተገኙ። ሊጋባ ወልደ ገብርኤ ል በሻህና አጋፋሪ መርዕድ ማርያም የቦታውን ወሰን እየረገጡና ምልክት*

ዛሬ በዕድገት የተራመዱ ሀገሮችን የተፋጠነ ልማትና ሥልጣኔ ሂደት ስንቃኝ መሠረቱ ለቀደመው ታሪካቸው የሰጡት ከፍተኛ ተኩረት እንደሆነ መገንዘብ ከባድ አይደለም። «ሮማ በአንድ ቀን አልተገነባችም» እንዲሉ የዘመኑ ድንቅ የሥልጣኔ ውጤት የአንድ ትውልድ ሥራ ሳይሆን የአያሌ ተከታታይ ትውልዶች ብርቱ ጥረት ድምር መሆኑን ያሣየናል። የቀደመ ታሪኩን እየጣለና እያፈረሰ አዲስ ታሪክ ብቻ በመገንባት ከፍተኛው የሥልጣኔ እርከን ላይ የተቆናጠጠ ሕዝብ ወይም ሀገር የለም።

ወደራሳችን ታሪክ መለስ ብለን ስንቃኝ ደግሞ አንዳንድ ተጻራሪ የሆኑ ሁኔታዎችን እናስተውላለን፣ ቅርሶቻችንን ራሳችን እየሠረቅንና ወደባዕዳን እጅ እያሻገርን ቅርስ አልባ እየሆንን መሄዳችን አንዱ አሳሳቢ ችግራችን ነው። ሌላው ጉዳይ ወጤ ቱን ሳናጤን የታሪክ መሠረታችንን እየናድንና እያጠፋን አዲስ ታሪክ ለማቆም መቻኮላችን ለታሪክ ወቀሳና ክሰሳ እየዳረገን መሆኑን በቅጡ አ ለማስተዋላችን ነው። በዚህ አኳያ



አቡነ ማቴዎስ



www.ethiopianorthodox.org

እያስቀመጡ ቀደሙ፣ ካህናቱም ከዚያ ቀጥለው ተከተሉ:: አፈንጉሡ ነሲቡና ከመኳንንት ሽማግሌዎች ከፍ ካለ ደልዳላ ሥፍራ ላይ ተቀምጠው የቅርቡን በዓይን፣ የሩቁን በመነጽር ይመለከቱ ጀመር:: ለምስክርነት የተ መደቡት ሰዎች ግን በወሰኑ ላይ አብ ረው ተጓዙ::

የወሰኑ ምልክት ከጃንሆይ ጉተራ በስተምስራቅ በኩል ከሚገኘው ቦታ ላይ ተጀምሮ የራስ ሚካኤል መኖሪያ ቤት ወደ ራጉኤል፣ የከንቲባ ወልደ ጻዲቅን ቤት ወደ ማርያም አስቀርቶ ወሰኑ በመካከሉ ላይ አለፈ:: ከዚያም ወደሰሜን አልፎ የደጃች ለየሀን ቤት ወደማርያም፣ የጦረኛ ወልደየሰን ቤት ወደራጉኤል አድርጐ ወንዙን ተሻግሮ ወደሱሉልታ አቅጣጫ ከሚያሣየው ከገደሉ አፋፍ ደረሱ:: ከዚያም የአ ፍፉን ጠርዝ ተከትለው ወደ ኋላ ታጠፉና ሸንቁሮ ከበሩ ላይ ቆሙ:: ከዚህ በኃላ የክሳላው ፍጻሜ ሆነና ወሰን ከሳዮቹ አውራውን መንገድ ተ ከትለው ወደማርያም ተመለሱ በማለት በወቅቱ የተጻፈው ታሪካዊ ማስረጃ ያትታል::


ሌላው አስደናቂ ሁኔታ በወሰን ክሰላው ወቅት በሁለቱ አድባራት ለምስክርነት ስለቀረቡት ሰዎች የተ ጻፈው ታሪክ ነው:: የወሰን ክሰላው ሥራ ሲጀመር ሊጋባ ወልደ ጉብርኤል ምስክር የሚሆኑላቸውን ሰዎች እንዲያቀርቡ የሁለቱን አድባራት አ ለቆች አዘዙ:: የራጉኤል ደብር አለቃ ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ በበኩላቸው የአገር ሽማግሌዎችን መርጠው አቀረቡ:: የማርያም ደብር አ ለቃ መልአከ ፀሐይ አፈወርቅ ከ15 ዓመት ያልበለጠ ዕድሜ ያላቸውን ልጆች አቅርበው በእኛ በኩል ምስክሮ ቻችን እነዚህ ናቸው አሉ:: ሊጋባ ወልደ ገብርኤልም ተደንቀው ሽማግሌ ሰዎች አለማቅረብዎ በምን ምክንያት ነው ብለው ቢጠይቋቸው፣ ሽማግሌ ሰ ዎች ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዕድሜ ውሳኔ ደርሶባቸው በሞት ያልፋሉ እነዚህ ህጻናት ግን በዕድሜ ይቆያሉ፣ ለማስታወስም ቢሆን የህጻናት አእምሮ የበለጠ ያስታውሣልና ብለው መለሱላቸው:: ሊጋባውና መኳንንቱም እውነት ነው ብለው ሀሣቡን ተ ቀብሏቸውና እነዚያ ህጻናት ምስክሮች ሆነው አብረው እንደተጓዙና የዚህም ታሪክ ፀሐፊ ከህጻናቱ መካከል አንዱ እንደነበር መርስዔ ሐዘን ወልደቂርቆስ «በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ካየሁትና ከሰማሁት» በማለው መጽሐፋቸው ገልጸውታል::»

በዚህ አጋጣሚ ሊታወስ የሚገባው ሌ ላው መንፈስን የሚነካው አስደናቂ ጉዳይ የራጉኤል ጽላት ነባር ቤተ መቅደሱን ለቆ ወደ አዲስ አበባ ከተማ በተጓዘበት ዕለት የርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያም አስተዳዳሪ የነበሩት መልአከ ፀሐይ ዘሰቀ የእንጦጦ ማርያምን ደውል አስደውለውና ሕዝብ ሰብስበው ዛ ራጉኤል ወርዷል ማርያም ብቻዋንሬ ቀርታለች ደ ረታችሁን ደቁ አልቅሱ፣ ብለው ሕዝቡን በእምባ በማራጨት ያሣዩት ተቆርቋሪነት ለሁለቱ አ ድባራት አንድነት ተጠቃሽ ምሳሌ ነው:: ለእንጦጦ ማርያምና ለእንጦጦ ራጉኤል መንትያነት ከዚህ የተሻለ ስሜትን የሚነካ ማስረጃ አ ይገኝም:: አባቶች ትተውልን የሄዱት ይህ በአንድነትና በፍቅር ተሳስሮና ተ ደጋግፎ የመሩ ሂደት ዛሬም በተ ጠናከረ መንገድ መቀጠል ይርበታል::

ቅርስ ለሆኑት አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ትኩረት በመስጠት እንክብካቤ ማድረግ በእንክሮ ሊታሰብበት የሚገባው ነው:: እዚህም ላይ በሥልጣኔ ከቀደሙት ሀገሮች ትንሽ ምሳሌዎችን መጥቀስ አስፈላጊ ሆ ይታያል:: በአደጉት አገሮች ከክርስቶ ስ ልደት በፊትና በኋላ ተመስርተው ዕድሜ የጠገቡ

ርሶች ችግር ሳያጋጥማቸው አ ልዘለቁም:: የተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች የመሬት መንቀጥቀጥ፣ እሣተ ገሞራ፣ አውሎ ንፋስ፣ ማዕበል፣ እየመታቸው፣ በየዘመኑ በተካሄዱት ጦርነቶች ከሰማይና ከምድር በሚወርወሩ አ ረሮች እየተቃጠሉ የፈረሱ ጥቂቶች አይደሉም:: ትውልዱ ግን የቅርሶቹን ውድመት በቸልታ ሳይመለከት፣ አእምሮውን ጨምቆ ሀብቱን አሟጦ እንደነበሩ መልሶ የገነባቸውና ከማንኛውም ሀብት በላይ አክብሮ የያዛቸው የታሪክ ቅርሶች አያሌ ናቸው:: ወደሀገራቸው ለሚሄዱት እንግዶች በቅድሚያ የሚያሣዩትም እነዚህን የመሳሰሉ የታሪክ ሥፍራዎችን ነው:: ለእኛም ይህ ተግባር በአርአያነቱ ትልቅ ፋይዳ አለው::

ቅርስ የህልውናችን መታወቂያ፣ የማንነታችን መግለጫ መሆኑን ከልብ አምነን በመቀበል ለቅርሶቻችን የምናደርገው ጥንቃቄና አክብሮት ባህላችን ሊሆን ይገባል:: እንጦጦ ራጉኤልንም በዚህ መልኩ ተረባርበን ከተንከባከብነው የጠፋውን ካደስነው፣ የጐደለውን ካሟላነው ወደነበረ ክብሩ መመለስ ብቻ ሳይሆን እንጦጦን የቱሪስቶች መናኸሪያ ማድረግ የማንችልበት ምክንያት ሊኖር አ ይችልም::


ITALI ROMA NO. 5805 = 1935

የሠነዱ ኮፒ በመልዕክ ኃይል አባ ወልደ ገብርኤል ወልደ ሳሙኤል ትጋትና ጥረት ከጣልያን አገር የተገኘ ነው::


www.ethiopianorthodox.org

# አለቃ ገብረሐና የመጀመሪያው የእንጦጦ ራጉኤል የአቋቋም መምህር

አለቃ ገብረሐና በጐንደር ክፍለ ሀገር፣ በደብረ ታቦር፣ አውራጃ፣ ከጣና ሐይቅ በስተምሥራቅ በምትገኝ በፎገራ ወረዳ፣ ልዩ ስሟ የናባጋ ጊዮርጊስ በምትባል ቦታ ከአባታቸው ከአቶ ደስታ ተገኘና ከእናታቸው ከወ/ሮ መልካሜ ይልማ በ1814 ዓ.ም በኅዳር ወር ተወለዱ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም በአቅራቢያቸው በሚገኘው የናባጋ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ትምህርት ቤት ገብተው ፊደል ከቆጠሩና ዳዊት ከደገሙ በኋላ በዜማ ቤት ጥቂት ጊዜ ቆይተው ጐጃም ክፍለ ሀገር በመሄድ የቅኔ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ። ከቅኔ ቤት እንደተመረቁ ጐንደር ተመልሰው በመምህራቸው መምህር ወልደ አብ ወልደ ማርያም አማካኝነት ሙሉ ጽዋተ ዜማንና ከመምህራቸው ከባህታዊ ገብረ አምላክ አቋቋምን ተማሩ። አለቃ ገብረሐና ከመምህር አካለወልድ ጋር አብረው የተማሩ ሲሆን መምህራቸው ወልደአብ ወልደማርያም "ገብረሐና ይህን ቀል ድህን ተው፣ አንተ ትልቅ ሰው ነህ፣ ብዙ ተምረሀል"እያሉ ደጋግመው ቢመክሯቸው አልሰማ ስላሏቸው አንተ በቀልድህ ተጠራ" እንዳሏቸውና መምህር አካለወልድን ግን በጾም በጸሎትም የታወቁ ስለነበሩ "ስምህ በየቤተክርስቲያኑ ሲጠራ ይኖራል" ብለው እንደመረቋቸውና አሁንም በየቤተክርስቲያኑ ስማቸው በመጠራት ላይ እንዳለ ካህናቱ ይናገራሉ።

አለቃ ገብረሐና በአጠቃላይ ድጓን ቅኔን የመጻሕፍት ትርጓሜን ማለትም አራቱን ጉባኤ መጽሐፈ መነኮሳት፣ መጽሐፈ ሊቃውንት፣ መጽሐፈ ብሉያትና መጽሐፈ ሐዲሳትን ተማሩ። በመምህሮቻቸው ትምህርት ብቻም ሳይወሰኑ አቋቋምን፣ ዝማሜን፣ ጸናጽል አጣጣልንና እንዲሁም ሌላውን በራሳቸው ጥረት ራሳቸውን እያስተማሩ ተወዳዳሪ የሌላቸው ሊቅ ሆኑ።

ቀደም ባለው ዘመን የነገሥታቱ ካልሆነ የምሁራኑንና የታዋቂ ሰዎች ታሪክ መጻፍ ያልተለመደ ነበርና ስለ አለቃ ገብረሐና ማንነትም ሳይጻፍ ቀርቶ መላ ታሪካቸውን ማወቅ አልተቻለም።

ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ የህይወት ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው የጥንት ምሁራንን ታሪክ መጻፍ ያልተለመደ መሆኑን አስመልክተው እንዲህ ይላሉ።

"በዚህ ዘመን ውስጥ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት ወገን እንደጊዜው ብዙ ዕውቀት የነበራቸውና ለመንግሥታቸው ብዙ ሥራ የሰሩ እጅግ ሰዎች ሳይኖሩ አይቀሩም ነበር። ነገር ግን እንደዛሬው ዘመን ነገሩን ሁሉ እየጻፉ ማስቀመጥ አልተለመደም ነበርና ስማቸው በታሪክ ተጽፎ ያገኘናቸው ጥቂቶች ናቸው። አንድ አንድም ወሬአቸው ቃል ለቃል ሲነጋገርላቸው እስከ እኛ ዘመን የደረሰላቸው አሉ።"

ሆኖም ከሌላ ታሪኮች መካከል የአለቃን ምሁርነት አስመልክተው ቅንጭብጫቢ ታሪኮቻቸው በአንዳንድ መጻሐፍት አልፎ አልፎ ተወስተው እናገኛለን። "በመጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ" አለቃ ለማ ሲናገሩ፡-

"አለቃ ገብረሐና የምያ መጨረሻ አይደሉም ወይ? የሐዲስ መምህር ናቸው። ፍትሐ ነገስት በሳቸው ልክ የሚያውቅ የለም። ይኸ ቁጥሩን፣ መረሐዕውሩን፣ አቡሻክሩን ሁሉ የሚያውቅ ባለሙያ ነው።

አለቃ ገብረሐና መቸም ኃይለ ቃላቸውና ስድባቸው የታወቀ ነው። የነገር ሁሉ ምንጭ መቸም ለዚህ ለዝማሜ እሚባለው ለመቋሚያ እገሌ ይመስለዋል አይባሉም። ገብረሐና ፊት የሚዘም የለም።"

ይላሉ ። አለቃ ገብረሐና ሰፋ ያለ አመለካከት ነበራቸውና ሰዎች አንድ ነገር አበላሽተው ሲሰሩ ካዩም ከመተቸት ወደ ኋላ አይሉም። አለቃ ያዩትን፣ የሰሙትንና የተሰማቸውን ከመናገር ስለማይቆጠቡ ተሳዳቢ ነበሩ የሚሏቸው አልጠፉም። ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ "የሕይወት ታሪክ"በሚለው መፅሐፋቸው የአለቃ ገብረሐናን ሊቅነት በማስመልከት እንደሚከተለው ጠቅሰውታል።

"አለቃ ገብረሐና እጅግ የተማሩ የጐንደር ሊቅ ነበሩ። በዚህ ላይ ደግሞ ኃይለ ቃልና ጨዋታ ያውቁ ነበር" ። በእርግጥም አለቃ በምሳሌያዊ፣ በሰምና ወርቅ አነጋገር ችሎታቸው እንዲሁም በብልሃትና በቀልድ አዋቂነታቸው የታወቁ ነበሩ። ለዚህም Leven Donald" wax and Gold" በሚለው መጽሐፋቸው የሚከተለውን እንመልከት. Alaqa Gabra Hanna Become most famous, however, forquick and biting wit. So prolific and beloved were his witticisms"

አለቃ ገብረሐና የአቋቋም፣ የቅኔና የመጽሐፍት ትርጓሜ መምህርም ነበሩ። ጉባኤ ዘርግተውም አስተምረዋል።

## የተክሌ አቋቋም

ዛሬ በየገዳማቱና በየአድባራቱ ቤተክርስቲያኖች በሙሉ የተክሌ አቋቋም በመባል የሚታወቀው የዝማሜ ትምህርት ማን ፈጠረው? እንዴትስ ተፈጠረ? የሚሉትን ጥያቄዎች ብናነሣ የተክሌ አቋቋም ተብሎ የሚጠራው የመጀመሪያ ፈጣሪ አለቃ ገብረሐና ሆነው እናገኛቸዋለን። አፈጣጠራቸውም አካባቢያቸው በሸምበቆ የተከበበ ስለነበር ሸምበቆው በንፋስ አማካኝነት እየተረዳ ሲወዛወዝ ተማርከው በዝማሜ ጊዜ የሰው ልጅም በዚህ አምሣል መወዛወዝ አለበት በማለት ነበር።

አለቃ ገብረሐና ስልቱን በመጠበቅ በሚገባ ራሳቸውን ካስተማሩ በኋላ በጐንደር ለሚገኙት ካህናትና ተማሪዎቻቸው ማስተማር ጀመሩ፣ ሆኖም ጐንደሮች ሲያገለግሉ ሸማቸውን ታጥቀው ስለነበር በሚያዘሙበት ጊዜ በተመስጦ ወዲያና ወዲህ ሲሉ ሸማቸውን እያስጣለ ቢያስቸግራቸው የጐንደር ሊቃውንት ስብሰባ አድርገው "ይህ ሸማ እያስጣለ የሚያስቸግር ስለሆነ አያስፈልገንም፣ ተማሪዎችም መማር የለባቸውም" ተባብለው ተማከሩ። መምህር ገብረሐናም ጽምዐ-እጥ ሆነው ብቻቸውን ቀሩ። መምህር ገብረሐና በፈጠሩት ምትክ አጭር ዝማሜ እንዲዘሙ ተስማምተው በቤተክርስቲያን ውስጥ በአጭሩ ዝማሜ ሲጠቀሙ መምህር ገብረሐና ግን ራሳቸው በፈጠሩት የዝማሜ ስልት ቀጠሉበት። በዚህም የጐንደር ካህናት በጣም ተናደው ከብዙ ጊዜ ክስ በኋላ እንኳን በቤተክርስቲያን በውጪው ቢሆን ሲጠቀሙበት ከታዩ እንደሚቀጡበት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው።

መምህር ገብረሐና የፈጠሩት አዲስ የውዝዋዜ ስልት በካህናቱ ተቀባይነት እንዳጣ ሲያውቁ ጥሩነሽ ገብረሐና የምትባል ትንሽ ልጃቸውን ከሩቅ ሰው ሲመጣ ጠብቃ እንድትነ


www.ethiopianorthodox.org

ግራቸው አድርገው ልጃቸውን ተክሌን ማንም ሳያይ ቤት ዘግተው አስተማርዋቸው። በድርቡሽ ዘረፋ ጊዜ ተክሌ ሸሽተው ለንጉስ ሚካኤል ለፈረሶች ሳር አጫጅነት ተቀጥረው መከራውን ሲያሳልፉት ከቆዩ በኋላ አንድ ቀን ንጉስ ሚካኤል ተንታ ሚካኤል ሲያስቀድሱ፣ ተክሌ ወኔአቸው ተቀስቅሶ እጣነ ሞገር ላይ አባታቸው ያስተማሩዋቸውን ረጅም ዝማሜ ሲዘሙ ንጉስ ሚካኤል ተገርመው "የፈረሶቻቸውን ሣር አጫጅ እንደፈረስ ያገለግል ጀመር አይደለም እንዴ?" ብለው በመደሰት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ እግዚአብሄር እንዲያገለግሉ አደረጉ። የደብረ ታቦሩ ራስ ጉግሳ ወሌም ከንጉስ ሚካኤል ጋር ቤተዘመዳሞች ነበሩና ይህን ሰምተው ተክሌን እንዲሰጥዋቸው ለመንዋቸው። ወስደውም ደብረታቦር እየሱስ ቤተክርስቲያን ሾመው አስቀመጥዋቸው።

አለቃ ተክሌ በቤተክርስቲያን ሲዘሙ እምባቸው እየወረደ ነበርና "ይኸስ መልአከ እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም" እስከመባል ደርሰው ነበር። ራስ ጉግሳም መንፈሳዊ በመሆናቸው አለቃ ተክሌ ሲዘሙ ከመዘምራኑ መካከል ገብተው ዝማሜውን ጸናጽል እያያዙን በጥሞና እየተመለከቱ ፈጣሪያቸውን ያመሰግኑ ነበር። ለአለቃ ተክሌም የወርቅ መቋሚያና ጸናጽል ገዝተው ሸለሟቸው።

አለቃ ተክሌ ደብረ ታቦር እየሱስ ላይ ጉባኤ ዘርግተው አቋቋም መርገድና ድፋት ሲያስተምሩ የሌሎች ደቀመዛ ምሮቶች ሣይቀሩ እየተሳቡ መጥተው የሚያስተምሩበትን ቦታ አጥለቀለቁት።

በዚህ ሁኔታ በአለቃ ገብረሐና ተፈጥሮ የነበረው አዲስ የውዝዋዜ ስልት በጐንደር ካህናት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ብቻ ልጃቸው አለቃ ተክሌ ደብረ ታቦር በግልጽ አስተምረው ወደ ሌላ እንዲዛመት አደረጉ።

ይህን የአቋቋም፣ ዝማሜንና ጸናጽል እውቀት ልጃቸው አጉልተው ቢያስተምሩም እንዲስፋፉ መሠረቱን የጣሉና ውዝዋዜውን ከዝማሜው አሠራርና አያያዝ እንዲሁም ከዜማው ጋር አዋህደው የፈጠሩት ሊቅ አባትየው አለቃ ገብረሐና ናቸው።

በ1840 ዓ.ም መግቢያ ላይ አለቃ ገብረሐና ጐንደር ውስጥ ሊቀ ካህንነት ተሹመው ለሰባት ዓመታት ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ ፍትሐ ነገስት አዋቂ በመሆናቸው በዳኝነት ተሹመው ተቀመጡ። በዚህም ጊዜ ፍርድ አዋቂ ነበሩና ማንኛውም ነገር ተናግረው የማሳመን ችሎታ ነበራቸው። ነገር በማሳመር በቀልድና በስብከት ችሎታቸው የሚወዳደራቸው ጠፉ። ከፍተኛ ስብከቶችንም አለቃ እንዲያካሄዱ ይመረጡና ይለመኑ ነበር።

አለቃ ትምህርታቸውና ዕውቀታቸው ከማንም በላይ እንጂ በታች አልነበረም። በዘመናቸው ተረትና ምሳሌ አፍላቂ፣ ቀልድና ንግግር አዋቂ በመሆን እንደበታቸው የስላው እጅግ የተማሩ ሊቅ በመሆናቸው ጭምር ነው። አለቃ ምንም እንኳን ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው ሊቅ ቢሆኑም በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በስፋት የሚታወቁት በትምህርታቸውና በሊቅነታቸው ሳይሆን በቀልደኛነታቸው ሆኖ ቀርቷል። በሌላ በኩል ራሳቸውም ቢሆኑ ባላቸው እውቀት በመጠቀም እውቀታቸውንና ትምህርታቸውን ለተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ያሰፈሩት ነገር አልነበረም።

አለቃ ገብረሐና በራስ አሊ (ትንሹ) ዘመነ መንግሥት በቤተ መንግሥት ውስጥ አጫዋች ነበሩ። አፄ ቴዎድሮስ አማቶቻቸውን ድል አድርገው አልጋውን ከወረሱ በኋላ እንደ በፊቱ ለመቀለድና ለመጫወት አልተመቻቸውም።

አፄ ቴዎድሮስ አለቃን በሙያቸው ቢወዷቸውና ቢያከብሯቸውም ቀልድና ፌዝ ስለማይወዱ "ፍታነገስቱንም ጻፍ፣ ፍርድም ሰጥ፣ ገንዘብም ያውልህ፣ ግን ቀልድህን ተወኝ" እያሉ ይመክሯቸው ነበር። በነበራቸው ክብርም መሠረት ከምኒሊክና ከእቴጌ ምንትዋብ ቀጥለው ግብር ላይ ተቀማጭ አለቃ ገብረሐና ነበሩ። ከዳግማዊ ምኒሊክ ጋር በመጀመሪያ የተዋወቁትና የተለማመዱት በዚህ ቤተ መንግሥት ነበር። እቴጌ ምንትዋብ ከሞቱ በኋላ የአፄ ቴዎ ድሮስም ጠባይ እየተለወጠ በመምጣቱ፣ አለቃም ቀልድን አልተው በማለታቸው አለመጣጣሙ እየከረረ ሄደ።

አፄ ቴዎድሮስ በቀልድ ምክንያት ከአለቃ ጋር መጣጣም ስላልቻሉ ከፊታቸው እንዲርቁላቸው ከፍርድ ሰጭነታቸው አስነስተው ትግራይ ጨለቆት የሥላሴ አስተዳዳሪ አድርገው ላኩዋቸው። በኋላም ካህናቱ በአፄ ቴዎድሮስ ላይ እንዲነሱ ካሴሩት ዋናው አለቃ ገብረሐና ነበሩና አፄ ቴዎድሮስ እንዲታሰሩ ስለአዘዙ አለቃ ሸሽተው በአንድ ገዳም ውስጥ ተሸሽገው አባ ተብለው ይኖሩ ነበር።

አባ ገብረሐና ከተሸሸጉበት ገዳም የወጡት አፄ ተድሮስ ከሞቱ በኋላ ነበር። ከዛም እንደወጡ በመጀመሪያ የሚካኤል ደብር በኋላም የአቡነ ሐራ ገዳም አስተዳዳሪ ሆኑ። አቡነ ሐራ በጣም የተከበረ ገዳም ነበር። በዚህ አቡነ ሐራ ድንግል ከሚገኘው ገዳም ሲያስተዳድሩ የአገሩ ህዝብ በችግር ላይ ስለ ነበር ለቤተክርስቲያኑ ከገባው የስለት ገንዘብ አንድ ሺህ ብር አንስተው ለካህናቱም ለባላገሩም አከፋፈሉ። በዚህም ምክንያት የስለቱን ገንዘብ "ለራሳቸው በልተው ለሌላው አብልተዋል" ተብለው አዲስ አበባ እፈንጉስ ነሲቡ መስቀሉ ዘንድ ክስ ተመስረተባቸውና ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው መጡ። ቀርበውም ቢጠየቁ "በክፉ ቀን ህዝቡ ስለተቸገረ ለህዝብ አከፋፍየዋለሁ" ብለው የእምነት ቃላቸውን ሰጡ። እፈንጉስ ነሲቡም "በላሁት ትላለህ? ክፈል" ቢሏቸው" እንደ ምጥዋ ዕቃ በነሲብ አልሸጥ ከየት አመጣለሁ" አሉዋቸው። እፈንጉስ ነሲቡም ጋሾ የሚባለውን ሰው የማንገላታት ልምድ ያለውን አሽከራቸውን ጠርተው "ጋሾ ዝም ትለኛለህ?" አሉት። ሊቀ መኳስ አባተ ቧያለው አጠገባቸው ነበሩና " ምንም እኔ ባላውቃቸው ጃንሆይ የኛ ህን ሰውዬ ክብር ሲናገሩ ሰምቻለሁ በኋላ ትጣላላችሁ። "ስላልዋቸው ከማስገፋቱ ተቆጥበው" የጐንደሩ ቀልደኛ ይኼ ነው? ብሉይና ሐዲስ የሚተረጉመው?" ቢሉ አለቃ እንግዲያው አልዩ አምባ ነው? አሉዋቸው"። (አልዩ አምባ የእፈንጉስ ነሲቡ አገር ሲሆን ምንም ዓይነት ትምህርት የማይታይበት የባርያ መሸጫ ነበርና መሳደባቸው ነበር።

እፈንጉስ ነሲቡ ወሬአቸውን በመቀየር ታዲያ ምን ይሻላል ምን ትላለህ ቢሏቸው "ይግባኝ ለጃንሆይ እላለሁ" አልዋቸው።

ዳግማዊ ምኒሊክ ዘንድ ቀርበው እፈ ንጉስ ነሲቡ "እኚህ ቄሶች የቤተክርስቲያኑን ገንዘብ በልቶብናል በማለት ከሰው እሱም መብላቱን አምኖአል። ክፈልም ብለው በክፉ ቀን ለህዝቡ አካፍያለሁ ብሎ መልስ ሰጥቷል" በማለት አስረዱ። ዳግማዊ ምኒሊክም "ቁርንጮ አፍ አንተ የምትለው እሳቸውን ነው?" በማለት እፈንጉስ ነሲቡን ተቆጥተው "ጌታ አለቃ ገብረሐና እርሶስ የፍታነገሥቱን ፍርድ አዋቂ አልነበሩም? እርሶ ያስረዱና "ቢሏቸው አባ ገብረሐናም" ፍታነገስቱማ

ጃንሆይ ከገባው ብጸት ሲሶውን ለካህናት፣ ሲሶውን ለሠራያን ይገባል ይላል። ስለዚህም እኔ ክፉ ቀን ስለሆነ ለህዝቡ እካፍየዋለሁ። አቡነ ሐራ አባታቸውን አይጦሩት፣ ልጃቸውን አይድኑበት፣ ገንዘቡ ተቀምጦ ምን ይሆናል? ብዬ ነው። ብቻ ጃንሆይ ከነሲቡ ምላጭ ያድንም" አሉዋቸው። ዳግማዊ ምኒልክም በፍርዳቸው ተደስተው፣ ራጉኤል አካባቢ ቤት አስርተውላቸው አቋቋምና መርገድ እያስተማሩ እንዲቀመጡ ለምነዋቸው። አባ ገብረሐና አምስት ዓመት አዲስ አበባ እያስተማሩ ከኖሩ በኋላ ወደ ጐንደር ከተማ ተመለሱ።

ዳግማዊ ምኒሊክ እንኳን አለቃ ገብረሐና በጊዜው የነበሩትን ምሁራንና ሊቃውንትን ይወዱ ነበርና አለቃ ገብረሐና ሥራቸውንና አገራቸውን ለቀው ሸዋ እንደገቡ በዳግማዊ ምኒሊክና በባለቤታቸው ተወዳጅነት አትርፈው የራጉኤል ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው ለኑሮአቸው ሆነ ለጨዋታቸው ምቹ ጊዜ ተፈጥሮላቸው ከመኳንንቱ ሳያንሱ በቤተ መንግሥቱ እንደ ከፍተኛ ባለ ማዕረግ ሆነው ኖሩ።

አለቃ ገብረሐና የዳግማዊ ምኒሊክ አማካሪ ነበሩ። ዳግማዊ ምኒሊክ አለቃን ሳያማክሩ ምንም ነገር አይሰሩም ነበር። በተለይም አለቃ ዳግማዊ ምኒሊክን ቅዳሜ ቅዳሜ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓተ ቤተ መንግሥትን ያስተምሯቸው ነበር። በቤተ መንግሥትም በሚደረገው ግብዣ መኳንንቱን ሁሉ ቀልድ በተሞላበት ህብር ንግግራቸው ሁሉንም በማሸነፍ ስለሚረቱ በየጊዜው ይሸለሙ ነበር። በብልሃታቸውም ሆነ በንግግራቸው የማ.በልጣቸው ቀርቶ የሚስተካከላቸው በመጥፋቱ ንጉሱም፣ ንግሲቲቱም፣ መኳንንቱም፣ ሌሎችም ይደነቁ፣ ይገረሙ ነበር።

አንድ ቀን ንጉሱና መኳንንቱ ተማክረው ለሚቀጥለው የግብዣ ቀን አንድ አንድ እንቁላል ይዘው እንዲመጡና አለቃ እንዳይሰሙ በሚስጢር እንዲያዝ አደረጉ። በግብዣው ቀን ሁሉም ይዘው መጥተው "ዛሬ ደግሞ ምን ይናገሩ ይሆን፣ ዛሬስ ይረታሉ፣ መቀጣታቸው አይቀርም በማለት እርስ በርሳቸው ሲንሾካሾኩ አጋፋሪው እንደተባለው "በዛሬው ቀን እሁኑኑ አንድ አንድ እንቁላል ካልወለዳችሁ ይፈረድባችኋል። " በማለት ጮክ ብሎ ተናገረ። በዚህ ጊዜ ሁሉም አውጥተው አስረከቡ። አጋፋሪው የሁሉንም ተቀብሎ የሁሉም ዓይን ወዳረፈበት በመዞር "ያምጡ እንጂ አለቃ እርሶ ብቻ እኮ የት የቀሩ" ቢሏቸው እጅሬ በርኖሳቸውን መታ መታ በማድረግ "ኩኩሉ፣ ይህን ሁሉ እንቁላል ያስጣልኩት አውራው እኔ ነኝ" አሉና የሁሉንም አፍ አስይዘው ረትው ሄዱ ይባላል።

አለቃ ገብረሐና ዳግማዊ ምኒሊክ ሆኑ እቴጌ ጣይቱ ይወድዋቸው እንደነበር ባይካድም እቴጌ አንድ ጊዜ በጣም ተቀይመዋቸው ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት ምንም እንኳን የአለቃ ሥራና ንግግር በሌላ ላይ ሲሆን ቢያስደስታቸውም አለቃ ግን እቴጌንም ባለመማራቸውና እቴጌም ብዙም ቀልድ የማይወዱ ስለነበሩ ከአለቃ ጋር ስላልተሰማሙ ምኒሊክ ሳይወዱ ወደ አገራቸው ጐንደር እንዲመለሱ አደረጉ።

አለቃ ገብረሐና ጐንደር ሄደው ትንሽ ከቆዩ በኋላ ልጃቸው ተክሌን "አዲስ አበባ ሄደህ አባቴ አለቃ ገብረሐና ሞተዋል ብለህ ነገርና ለተስካር ማውጫ የሚሆን ገንዘብ አምጣልኝ ብለው ላኩት እሱም ወደ አዲስ አበባ መጥቶ አባቴ አለቃ ገብረሐና ሞቱ "ብሎ ለዳግማዊ ምኒሊክ እያለቀሰ ነገራቸው። ዳግማዊ ምኒሊክም በጣም በማዘንና በመጸጸት "ገብረሐና ሞተ! በል ለተዝካር ማውጫ ስጠው "ብለው ብዙ ገንዘብ አዘዙለት። ከሌሎች መኳንንት በተጨማሪ ተዋጥቶ ከሸኚ ጋር ለልጁ ተሰጠውና ጐንደር ገባ።

አለቃ በዚ.ያ ገንዘብ የሚያስፈልጋቸውን ነገር እየገዙ ከተጠቀሙበት በኋላ ገንዘቡ ሊያልቅ ሲል የጠጠረ በቅሏቸውን ገዝተው በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ወዲያ ወዲህ ሳይሉ ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ። ጊቢ እንደደረሱ ሊገባ ወልደ ገብርኤልን አግኝተው ከተሳሳሙ በኋላ አለቃ "እኛኮ ሞቱ ተብሎ ተነግሮን ነበር" አሉዋቸው። አለቃም እባክህ ምን እሞታለሁ ይልቅ ለጃንሆይ ግባና ንገርልኝ አሏቸው "እያምኑኝም" ቢሉዋቸው አለቃም "ብቻ አንተ ገብረሐና መጥተዋል ብለህ ንገርልኝ ጃንሆይ አይተው ገብረሐና አይደለም ብለው ይመልሱኝ" አሏቸው። ሊጋባ ወልደ ገብርኤል እንደ ተባሉት ገብተው ሲናገሩ"ወለፍላፋ ከሞተ ስንት ጊዜው"! ቢሉ ምኒሊክ ይሙት መጥተዋል" አሉ። ኸረ አንተ ድርቅ በል ሂድ እስቲ አረጋግጥ" ብለው በጊዜው ግምጃ ቤት የነበሩትን በጅሮንድ ይብሳን ልከው ካረጋገጡ በኋላ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ከንጉስ ጋር ተገናኙ።

ዳግማዊ ምኒሊክ ተደስተውና ተገርመው "ገብረሐና ሞተህ አልነበረም እንዴ? ያንተ ነገር፣ ከየት መጣህ"? አሉዋቸው። አለቃም "እዎ ጃንሆይ ሞቼ ነበር። ነገር ግን እዚያ ምኒሊክ የለ፣ ጣይቱ የለች፣ መኳንንቱ የለ፣ ጠጅ የለ፣ ጮማ የለ ባይ ሰማይ ብቻ ሲሆንብኝ ጊዜ ለበረኛው ግቡ ገንዘብ ሰጥቼ ጠፍቼ መጣሁ" አሉዋቸው። ደግማዊ ምኒሊክም አለቃ ሞተው የተነሱላቸው ያህል ቆጥረው በጣም ተደስተው ከእቴጌ አስታርቀዋቸው እንደገና አብረው መኖር ጀመሩ።

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ አብረው እየኖሩ ጥቂት ዓመታት ካሳለፉ በኋላ በ1897 ዓ.ም ወደ ጐንደር ተመልሰው ናባጋ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ገብተው ተቀመጡ። እዚያም "እግዚአብሔርን ላመሰግንበትና ልቀድስበት በተሰጠኝ አንደበቴ ዋዛ ፈዛዛ ስናገርበት ኖሬአለሁ። " በማለት አንደበታቸውን ከመናገር ከልክለው፣ የሚወዱትን አረቄና ጠጅ ትተው፣ ከጥሩ ምግብ ተቆጥበው፣ ሌሊት መሬት ላይ እየተኙ እምባ በማፍሰስ፣ ቀን ቀን ከብት እየጠበቁ ከእንሰሳት ጋር በመዋል አንድ ዓመት ንስሐ ገብተው ትህርምት ይዘው ካሳለፉ በኋላ ለጊዜው ሞታቸው አርባ ቀን እንደቀራቸው ሴት ልጃቸውን ወ/ሮ በፍታ ገብረሐናን አስጠርተው ስጋዬን የበላ፣ ደሜን የጠጣ የዘላለም ህይወት ያገኛል የሚለውን ስለማውቅ ሥጋወደሙን እንዲያቀምሱኝ፣ ለቀሳውስቱ ንገሪልኝ" ብለው በጽሑፍ በመንገር ስጋወደሙን ተቀብለው የካቲት 24 ቀን 1898 ዓ.ም በተወለዱ በ84 ዓመት ከሶስት ወር እድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ስርዓተ ቀብራቸውም በዚሁ በናባጋ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ተፈጸመ።

አለቃ ገብረሐና ምንም እንኳን እድሜአቸውን በሙሉ በቀልድ ቢያሳልፉም በጣም በበሰለ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታቸው የአማርኛ ቃላት በማበልጸግና በማዳበር ረገድ የማይናቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ ናቸው። ጐንደርንም እስከ አሁን ድረስ የአቋቋምና የትርጉም ትምህርት ቤት በመሆን የታወቀች እንድትሆን የረዱ አንጋፋ ሊቅ ነበሩ።

❁ ❁ ❁


www.ethiopianorthodox.org